እፕድ
# አዲስ ዘመን
ማክሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 010 መስከረም 10 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁ የውሃ አጀንዳ አቅጣጫን ያስቀይራል


ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ
ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቅ ግድቡ እንዳይሠራ ሲጥሩ የነበሩ የውጭ ጠላቶችን የውሃ አጀንዳ አቅጣጫ የሚያስቀይር መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለጸ።

የዓባይ ግድብ ባለፈው ዓመት ነሐሴ ወር ላይ 22 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ ይዞ በሁለት ተርባይኖች 750 ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ የዓባይ ግድብ የሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቁ የኢትዮጵያን የመደራደር አቅም ከፍ ከማድረጉም በላይ ግድቡ እንዳይሠራ ሲጥሩ የነበሩ ኃይሎችን የ "ውሃ መያዝ" አጀንዳ የሚያስቀይር ነው።

ከግድቡ ሶስተኛ ዙር ሙሌት በኋላ ግድቡን የሚቃወሙ ኃይሎች የሚያነሱት አጀንዳ ውሃ ስለመያዝና ስላለመያዝ አይሆንም ያሉት ሚኒስትሩ፣ የውሃ መያዝ ጥያቄው ቢነሳ እንኳን ለኢትዮጵያውያን የሚሠራ ጥያቄ አይሆንም ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፣ በግድቡ ዙሪያ እንደራደራለን የሚሉ ኃይሎች የሚያራግቡት የውሃ መጠን መቀነስን

ሶስተኛ ዙር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በ2015 የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ እንደሚሰሩ መምህራን ገለጹ

## - በትናንትናው እለት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ትምህርት ተጀምሯል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 የትምህርት ዘመን ካለምንም የዲሲፕሊን ግድፈት የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በጋራ እንደሚሰሩ መምህራን ገለጹ። በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍሎች በትናንትናው እለት ትምህርት ተጀምሯል፡፡

በኮከበ-ጽበሃ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ልማት ምክትል ርዕሰ መምህር አቶ ሙሉዓለም ኃይሉ በየካ ክፍለ ከተማ ከሚገኙ ሰባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ9ኛና 10ኛ ክፍል አዲስ የተካተቱ ትምህርቶች በሙከራ የሚሰጥበት መሆኑን ለኢትጵያ ፕሬስ ድርጅት ጠቁመዋል።

በትምህርት ቤቱ ከ9ኛ እስከ 12 ክፍል 3300 ተማሪዎች ምዝገባ አድርገዋል፤ በተለይ ከክልል የሚመጡ ተፈናቃይ ተማሪዎችን ቅድሚያ በመስጠት ለመቀበል ዝግጁ መሆኑንም ገልጸዋል።

በዘንድሮው የ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች እና መምህራን የቅድመ ዝግጅት ገለጻ መደረጉን ጠቅሰዋል።

በትምህርት ቤቱ ቅጥር ጊቢ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ተግባራት፣ ትምህርታቸውን በምን መልኩ መከታተል እንደሚገባቸው፣ እንዲሁም አዲስ የሚጀመሩ ትምህርቶች በምን መልኩ መከታተል

በ2015 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ
የእቴጌ መነን የልጀገረዶች አዳሪ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ








አቶ ገመቺስ መላኩ

# ዘንድሮ የውጭ ምንዛሪ ገቢን 5 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዷል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በ2015 ዓ.ም ከወጪ ንግድና ከተለያዩ የገቢ ማስገኛዎች 5 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ።

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የአጠቃላይ የወጪ ንግድ ዕቅድ አፈጻጸም መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ገመቺስ መላኩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት በዘርፉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ እመርታ እየታየ ነው።

በዘርፉ በሚስተዋሉ ማነቆዎች ላይ በቀጣይነት መፍትሄ በማበጀት ሀገራችንን ከውጭ ምንዛሪ ችግር ለማላቀቅ የተጀመረው ስራ ተስፋ ሰጪ መሆኑንም ገልጸዋል።

በሕግ ዙሪያ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት የሕግ ማዕቀፎች ዙሪያ ማሻሻያዎች ተደርገዋል ያሉት ስራ አስፈጻሚው፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጉምሩክ፣

ዘንድሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ገጽ 3
ደቡብ ኮሪያ ለአፍሪካ የግብርና ልማት ግማሽ ቢሊዮን ዶላር መድባ እየሰራች ነው

# በጎባ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሪዎች ምገባ ተጀመረ

## - በክልሉ ከስምንት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ትምህርት ጀምረዋል

ዳግማዊት ግርማ

ባሌ ጎባ፡- በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በያዘው እቅድ መሰረት በባሌ ዞን ጎባ ከተማ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሪዎች ምገባ መርሀግብር መጀመሩን የከተማዋ ከተማ አስተዳደር ገለጸ። አስተዳደሩ ከተለያዩ የከተማዋ ነዋሪዎችና በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ከ420 በላይ ደርዘን ደብተር የኑሮ ደረጃቸው አነስተኛ ለሆኑ ተማሪዎች ማሰባሰቡንም ገልጿል።

የጎባ ከተማ ከንቲባ አቶ ሽመልስ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ ለሚገኙ ከአንደኛ ክፍል እስከ አራተኛ ለሚገኙ የአንደኛ ደረጃ መንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የምገባ ሥርዓትን በያዝነው በጀት ዓመት የትምህርት ዘመን አስጀምሯል።

እንደ አቶ ሽመልስ ገለፃ፤ በመንግሥት በተመደበ በጀት ሳይሆን ሕዝብ ተሳትፎ በከተማዋ ትምህርትን በሚመለከት ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች በመከናወን ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ የተማሪዎች ምገባም የእንቅስቃሴው አካል ነው።

አንድም ተማሪ በሚበላው ምግብ እንዲሁም በመማሪያ ቁሳቁሶች እጥረት ከትምህርት ገበታው እንዳይሰናከል በማሰብ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን የገለጹት ከንቲባው፤ በመላው ኦሮሚያ ግዴታ ተደርጎ እንዲሁም ሁሉም ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎችን መመገብ እንደሚገባ ታምኖበት ስራዎች መሰራታቸውንም ገልጸዋል።

የምገባ መርሀገርብሩ በሕዝብ ተሳትፎ የሚከወን መሆኑን ያመላከቱት አቶ ሽመልስ የመመገቢያ ስፍራና ምግብ ትምህርት ቤት ውስጥ ተመግበው የሚውሉበትን መንገድ በማመቻቸት ወደ ስራ መግባቱንም ነው የተናገሩት።

ሕዝብን አሳታፊ ሆኖ ተግባራዊ የሚደረገው የምገባ መርሀግብር ተማሪዎች ሃሳባቸው ስለምግብ ሳይሆን ስለ ትምህርታቸው ብቻ እንዲጨነቁና ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚያግዛቸውም ነው አቶ ሽመልስ የተናገሩት።

የትምህርት ቁሳቁሶችንም በሚመለከት ከተማ አስተዳደሩ ስራዎችን ማከወኑን ያመላከቱት አቶ ሽመመል፤ ደብተሮች ቦርሳዎች ስኪሪፕቶና እርሳሶችም መሰባሰባቸውን ተናግረዋል።

አቶ ሽመልስ በገለፃቸው ከተለያዩ የከተማዋ ነዋሪዎቻቸውና በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ከ420 በላይ ደርዘን ደብተር የኑሮ ደረጃቸው አነስተኛ ለሆኑ ተማሪዎች መሰባሰቡንም አሳውቀዋል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሳ በበኩላቸው፤ ክልላቸው ለመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚሰጠውን የምገባ መርሀግብር የሀብት ማሰባሰቡን በማጠናቀቅ በመጪው ህዳር ወር ላይ አጠቃሎ ይጀምራል ብለዋል።

እስከዛው ድረስ ግን በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ምገባው መጀመሩን ጠቁመዋል። በትናንትናው ዕለትም ከስምንት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ትምህርት መጀመራቸውን ዶክተር ቶላ ገልጸዋል።

በኦሮሚያ ክልል ህዳር ላይ በሚጀመረው የምገባ መርሀ ግብር ላይ ከሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለሚበልጡ ተማሪዎች ምገባ እንደሚደረግም ኃላፊው ጨምረው ገልጸዋል።



# 280 የገጠር መንደሮችና ከተሞችን የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት 280 የገጠር መንደሮችና ከተሞችን የኤሌክትሪክ ሃይል ተጠቃሚ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ እሱባለው ጤናው እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት ለ 1 ነጥብ 2 ደንበኞች አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግና 280 የገጠር መንደሮችና ከተሞችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሰራ ነው ።

በቀጣይ ሶስት ዓመታትም 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ደንበኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ግብ መቀመጡን አመልክተው፤ አገልግሎቱ በ2017 ዓ.ም በገጠር ለሚኖሩ ዜጎች ኤሌክትሪክ ለማዳረስ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

አገልግሎቱ የሶስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድን ዳግም በመከለስ ወደ ተግባር መግባቱን ዳይሬክተሩ ገልጸው በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ቤቶች የኤክትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል። በዚሁ መሰረት ከዋናው ግሪድ 65 በመቶ እና ከግሪድ ውጭ በፀሐይ ሃይል 35 በመቶ ኤሌክትሪክ ሃይል ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ መታቀዱን ገልጸዋል።

ተቋሙ የመሰረተ ልማት ስራዎችን በራሱ ወጪ ለመሸፈን የፋይናንስ ሞዴል መቀየር፣ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓትና አቅም ማጎልበት፣ የደንበኞች አገልግሎት እርካታ ለማምጣት እየሰራ ነውም ብለዋል።

የአማራ ክልል ኤሌክትሪክ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ አቶ ሰለሞን ጣሰው በበኩላቸው በዚህ ዓመት በክልሉ ከ200 ሺህ በላይ ደምበኞችን የሃይል አቅርቦት ተደራሽ ለማድረግ እየሰሩ መሆኑን ገልጿል።

የወልድያና የደሴ ዲስትሪክትን ጨምሮ በአሸባሪው ሕወሓት ጉዳት የደረሳባቸውን መስመሮች ጠግኖ ስራ ከማስጀመር ባለፈ 52 ተጨማሪ የገጠር ቀበሌዎች ባለፈው ዓመት አገልግሎቱን ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

በጥቅሉ ባለፈው ዓመት 76 ሺህ 300 ደንበኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን አመልክተዋል።

በዓመቱ የተሻለ የሃይል አቅርቦት ለማረጋገጥ፣ የሃይል መቆራረጥና የአገልግሎት መጓደል ለማስቀረት እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአፋር ክልል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ስራ አስፈፃሚ አቶ ያሲን አሊም እንዲሁ አሸባሪው ሕወሓት በመሰረተ ልማቱ ላይ ባደረሰው ጉዳት የሃይል አቅርቦት ላይ መስተጓጎል ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሰዋል። ጉዳት ከደረሰባቸው 18 ማዕከላት ውስጥ 12 የሚሆኑትን ጠግኖ አገልግሎት ማስጀመር መቻሉንም ተናግረዋል።

በተያዘው ዓመት በክልሉ የተቀሩትን 6 ማዕከላት ወደ ስራ ከማስገባት ጀምሮ ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን ኢዜአ ዘግቧል።

# የከተሞችን የቤት አቅርቦት ወደ 84 ከመቶ ለማሳደግ እየተሰራ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የከተሞች የቤት አቅርቦት ከ64 ከመቶ ወደ 84 ከመቶ ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን የከተማ ልማትና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ገለጸ።

የከተማ ልማትና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ሔለን ደበበ፤ መንግሥት ባለፉት ዓመታት የቤት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ሲያደርግ ቢቆይም አሁንም በርካታ ስራዎች እንደሚጠበቅበት ገልጸዋል። አሁን ላይ ያለውን 64 በመቶ የከተሞች የቤት ሽፋን ወደ 84 በመቶ ለማሳደግ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ይህን ያሉት የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከደቡብ አፍሪካው ዊትዋተርስራንድ ዩኒቨርሲቲ ጋር የሰሩት የወጣቶች ኑሮ ፣ የስራ ዕድል ሁኔታ፣ የመኖሪያ ቤት ጉዳዮችና ትስስሮች ምርምር ይፋ በተደረገበት መድረክ ነው።

በከተሞች የቤት ግንባታ ላይ ብዙ ወጣቶች ተሳታፊ ቢሆኑም እነርሱን ባለቤት ማድረግ ገና ብዙ ስራ እንደሚፈልግ ነው የተናገሩት።

ሚኒስቴሩ በቀጣዮቹ አስር ዓመታትም ከግል ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከአጋር ተቋማትና ምርምር ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ፤ ከመድረኩ የሚገኘውን ሃሳብ በመከለስ ለፖሊሲ ግብዓት እንደሚገለገልበት ገልጸዋል።

የሐዋሳ ከተማ ከንቲባ ረዳት ፕሮፌሰር ፀጋዬ ቱኬ ፤ ዩኒቨርሲቲው ለሚሰራው ስራና የመኖሪያ ቤት ትስስር የምርምር ስራ ከተማ አስተዳደሩ ከጎኑ መሆኑን ነው የተናገሩት።



የሐዋሳ ዩኒቨርሰቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር አያኖ በራሶ ፥ የምርምር ፕሮጀክቱ ዩኒቨርሲቲው ከውጭ ሀገር ተቋማት ጋር ከሚያካሂዳቸው 71 የትብብር ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ የሆነው ከሼፊልድና ዌትስ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጋራ የሚያከናውነው "ዩዝ ፊውቸር" የተሰኘ የምርምር ፕሮጀክት ነው ብለዋል።

በመድረኩ ላይ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር በከር ሻሌን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# ደቡብ ኮሪያ ለአፍሪካ የግብርና ልማት ግማሽ ቢሊዮን ዶላር መድባ እየሰራች ነው

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ደቡብ ኮሪያ ለኮሪያ- አፍሪካ የምግብና ግብርና ትብብር 500 ሚሊዮን ዶላር መድባ እየሰራች መሆኑን በኢትዮጵያ የኮሪያ አምባሳደር ካንግ ሲዮ ክሂ ገለጹ። ደቡብ የኮሪያ አፍሪካ የምግብና ግብርና ትብብር በአፍሪካ የሽንኩርትና ቲማቲም ምርትን ለማሳደግ ዓላማ ያደረገ ጉባኤ ትናንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

በኢትዮጵያ የደቡብ ኮሪያ አምባሳደር ካንግ ሲዮክሂ በጉባኤው መክፈቻ እንደገለጹት፣ በአፍሪካ በምግብ ዋስትና ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለመቀልበስ የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማነት ማሳደግ ወሳኝ ነው። ደቡብ ኮሪያ በግብርናው ዘርፍ ያመጣችውን ለውጥ በተሞክሮ መልኩ ለአፍሪካ አገራት ከማጋራት ባሻገር ውጤታማ እንዲሆኑ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ታደርጋለች ብለዋል።

ደቡብ ኮሪያ በግብርናው ዘርፍ ውጤታማ ያደረጋት የግብርና ቴክኖሎጂን በአግባቡ በመጠቀም መሆኑን የገለጹት አምባሳደሩ፣ በአፍሪካም ቀጣይነት ያለው የግብርና ውጤታማነት እንዲመዘገብ ቴክኖሎጂን መጠቀም አስፈላጊ ነው። አዳዲስ የአትክልናና ፍራፍሬ ዝርያዎችን በማራባት ምርትማነትን ማሳደግና በምግብ ዋስትና ላይ የተጋረጠውን አደጋ መቀልበስ ይገባል ነው ያሉት አምባሳደሩ።

ትብብሩ በአፍሪካና በደቡብ በኮሪያ መካከል ያለውን ወዳጅነት ለማጠናከር ወሳኝ ነው ያሉት አምባሳደር ካንግ፤ የግብርናውን ዘርፍ ማዘመን አስማማኝ የኢኮኖሚ እድገት ያመጣል። ለደቡብ ለኮሪያ ዕድገት መሰረቱ በ 1970 ዎቹ



ፎቶ - በሃይሉ አብርሃ

መጨረሻ በጥናት ላይ የተመሰረተ የግብርና ቴክኖሎጂን መጠቀሟ ነው። በዚህም የገጠሩንና የከተማውን አካባቢ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ግብርና በመስራት የማይቀለበስ የኢኮኖሚ ዕድገት እንድትመሰርት አድርጓታል።

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ አፍሪካ አሁን ላይ በዩክሬንና ሩሲያ ጦርነትና በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ በምግብ ቀውስ ውስጥ ትገኛለች። ከዚህ ቀውስ ለመውጣት ግብርናን ማዘመን ቁልፍ የአፍሪካ አጀንዳ አድርጎ መስራት ይገባል። ደቡብ ኮሪያ ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን 500 ሚሊዮን ዶላር መድባ ፕሮጀክቶችን ቀርጻ ትብብሩን እየደገፈች ነው። ፕሮጀክቱ ውጤታማ እንዲሆን አፍሪካውያን ትብብር ሊያደርጉ ይገባል። በአፍሪካ ግብርና ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ ደቡብ ኮሪያ ድጋፏን አጠናክራ ትቀጥላለች ብለዋል።

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ፈቶ ኢሰሞ በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ደቡብ ኮሪያ የዘመቱበትን በማስታወስ የኢትዮጵያ ኮሪያ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የረጅም ጊዜና ጥብቅ ቁርኝነት ያለው ነው። በደቡብ ኮሪያ ጦርነት የኢትዮጵያ ወታደሮች በመዝመት የሕይወት መስዋትነት እስከመክፈል ደርሰዋል። አሁን ደግሞ በግብርናው ዘርፍ በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ ደቡብ ኮሪያ ያላትን ውጤታማ ተሞክሮ ለአፍሪካ በማካፈል እያደረገችው ያላት አስተዋጽኦ የላቀ ነው።

እንደ ዶክተር ፈቶ ገለጻ፤ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ግብርና ለኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት ቢሆንም ምርታማነትን በማሳደግ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረገው ግን ብዙ ስራን የሚጠይቅ ነው። የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርታማነትን ማሳደግ ወሳኝ ነው።

በቲማቲምና በሽንኩርት ላይ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ስራዎች አንዱ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጫ መንገድ ነው ያሉት ዶክተር ፈቶ፤ በትብብር ፕሮጀክቱ ከ200 በላይ የቲማቲምና የሽንኩርት ዝርያዎችን ከደቡብ ኮሪያ በማምጣት በምርምር በማስደገፍ እየተሰራ ነው ብለዋል።

እንደ ደቡብ ኮሪያ ያሉ በቲማቲምና በሽንኩርት ውጤታማ የሆኑ አገሮችን ልምድ መካፈል ለአፍሪካ የምግብ ዋስትና መረጋገጥ ወሳኝ ነው ያሉት ዶክተር ፈቶ፤ አፍሪካውያን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የደቡብ ኮሪያን የግብርና ውጤታማነት ተሞክሮ ቀምረው ሊሰሩ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል። በጉባኤው በዘርፉ ያሉ ምቹ አጋጣሚዎችና ፈተናዎች ላይ በመወያየት ቀጣይ ውጤታማ የሚሆንበት መንገድ መቀየስ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

በጉባኤው ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ16 የአፍሪካ አገራት የተውጣጡ የግብርና ተመራማሪዎች የተገኙ ሲሆን የየአገራቸውን የግብርና ተሞክሮ አቅርበው ውይይት ተደርጎበታል።



## “የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ በሚደረገው ትግል ዜጎች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል”

### - አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ክብርና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ በሚደረገው ትግል ዜጎች ሁሉ የድርሻቸውን እንዲወጡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ ጠየቁ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣ ምክትል አፈ ጉባኤ ሎሚ በዶ፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ዘሃራ ሁመድ እንዲሁም ሌሎች የምክር ቤቶቹ አባላትና ሰራተኞች የተሳተፉበት ለሀገር መከላከያ ሠራዊት የደም ልገሳ መርሃ ግብር ተከናውኗል።

የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር በግንባር እየተዋደቀ ለሚገኘው የሀገር መከላከያ ሠራዊት በደም ልገሳ በገንዘብ በአይነት የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ገልጸዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፤ በደም ልገሳው ወቅት ባስተላለፉት መልእክት ኢትዮጵያ በመስዋትነት ፀንታ የኖረች በመስዋትነትም ጸንታ የምትቀጥል ሀገር መሆኗን ገልጸዋል። ለኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ሲል በግንባር እየተዋደቀ ለሚገኘው የሀገር መከላከያ ሠራዊት ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ የሁላችንም ግዴታ ነው ብለዋል።

የሁለቱ ምክር ቤቶች አባላትና ሰራተኞች የደም ልገሳ መርሃ ግብር ያደረጉትም ለሠራዊቱ አለኝታነታቸውን ለማሳየት መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያን ክብርና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ በሚደረገው ትግል ዜጎች ሁሉ በያሉበት የድርሻቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ ዘሃራ ሁመድ፤ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት ከደም ልገሳ በተጨማሪ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ ከዜጎች የሚጠበቅ ሃላፊነት መሆኑን ገልጸዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ሎሚ በዶ፤ አሸባሪው ሕወሓት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከውጭ ጠላቶችና ከውስጥ የጥፋት ቡድኖች ጋር እየሰራ በመሆኑ ሁላችንም በጋራ ለመመከት መነሳት አለብን ብለዋል።

የሀገርን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ በግንባር እየተዋደቀ ለሚገኘው ሠራዊት የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥልም መጠየቃቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

## በመዲናዋ በ699 የጤና ተቋማት ላይ እርምጃ ተወሰደ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የሕብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ሕግ ተላልፈው በተገኙ 699 ተቋማት ላይ እርምጃ መውሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ የምግብና መድሃኒት፣ የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የባለሥልጣኑ ጤና ዘርፍ ምክትል ዋና ዳሬክተር አቶ አምደየሱስ አድነው እንደተናገሩት፣ በአዲስ አበባ ያለውን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራቱን የጠበቀ ለማድረግ የተጠናከረ የብቃት ማረጋገጥና የቁጥጥር ሥርዓት አዘጋጅተን ወደ ሥራ ገብተናል። በዚህም በ699 ተቋማት ላይ እርምጃ ተወስዷል።

ሕብረተሰቡ የሚያገኘው የጤና አገልግሎት ደህንነቱ ተጠብቆ እንዲኖር ለማድረግ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል ያሉት አቶ አምደየሱስ፣ በጤና ቁጥጥሩ በተገኘው መሰረት በተቋማቱ ላይ የቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ የ3 ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ፣ የውስንና የሙሉ አገልግሎት እገዳ ተደርጎባቸዋል። በዚህም ሕብረተሰቡ የጤና መታወክ እንዳያጋጥመው በትኩረት እየሰራን እንገኛለን ብለዋል።

እንደ አቶ አምደየሱስ ገለጻ፣ 84 ተቋማት በቅድመ ማስጠንቀቂያ ፣ የ3 ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው 473 ተቋማት ሲሆኑ የውስንና ሙሉ አገልግሎት እገዳ የተደረገባቸው ደግሞ 142 ናቸው። በድምሩ 699 ተቋማት ላይ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያና እገዳ ተደርጎባቸዋል።

በቁጥጥር ስራችን ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው የመንግሥትና የግል የጤና ተቋማት ሀገር አቀፍ ስታንዳርድን መሰረት በማድረግ ያለባቸውን ክፍተት በመለየት እንደየደረጃቸው ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር እያደረግን ቆይተናል ብለዋል።

የሀገሪቷን ስታንዳርድ የጠበቁና በተሟላ ብቃትና ደረጃ ላይ የሚገኙ ተቋማትን ለመደገፍ ጥረት አድርገናል ያሉት አቶ አምደየሱስ፣ ባስቀመጥነው መስፈርት ሶስት ከመቶ በቀይ ደረጃ ፣ 34 ከመቶ በቢጫ እና 63 ከመቶ ደግሞ በአረንጓዴ ደረጃ ያሉ ናቸው። ባጠቃላይ 2 ሺህ 537 ተቋማት ላይ የክፍተት ስራ ተከናውኗል ብለዋል። የክፍተት ዳሰሳው የትኩረት ነጥቦችም ከሥነ-ሕንፃ፣ ከሙያ ትግበራ፣ ከግብዓትና ከባለሙያ አንፃር መሆኑንም ተናግረዋል።

እንደ አቶ አምደየሱስ ገለጻ፣ ከ2 ሺህ 537 ተቋማት


አቶ አምደየሱስ አድነው
የባለስልጣኑ ጤና ዘርፍ ምክትል ዋና ዳሬክተር

ውስጥ የቼክሊስቱን 50 በታች ያመጡትና በቀይ ደረጃ የተቀመጡ 77 ተቋማት ናቸው። ከ50 እስከ 75 ያመጡና በቢጫ ደረጃ የተቀመጡ ደግሞ 874 ተቋማት ናቸው። 1 ሺህ 586 ተቋማት ደግሞ በአረንጓዴ የተቀመጡና የአጠቃላዩን 63% የሚወክሉ ናቸው።

ከመደበኛ ሥራዎች አንፃር እርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ 86 የመድሃኒት ድርጅቶች ውስጥ 62 የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፤ 11 ጊዜያዊ እገዳና 1 የብቃት ማረጋገጫ ስረዛ ተደርጓል። 66 ሺህ 424 ኪሎ ግራም መድሃኒቶች ደግሞ በብር ግምታዊ ዋጋ 20 ሚሊየን 472 ሺህ 795 እንዲወገድ ተደርጓል።

አቶ አምደየሱስ አክለውም፣ ከ218 ጤና ተቋማት ውስጥ 138 የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 42 ደግሞ የብቃት ማረጋገጫቸውን የማገድና የማሸግ እንዲሁም ሁለት ብቃት ማረጋገጫ ስረዛና አንድ በሕግ ተጠያቂ የማድረግ ሥራ ተሰርቷል ብለዋል።

በ2015 በጀት ዓመትም እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን በማጠናከር በሀገሪቷ እየተመዘገበ ባለው ሁለንተናዊ እድገት ጤንነቱ የተጠበቀ ሕብረተሰብ እንዲኖር እንሰራለን ያሉት አቶ አምደየሱስ፣ በህክምና ስህተት ጉዳት ደርሶብኛል የሚል አካል ካለ ጉዳዩን ወደ ምግብና መድሃኒት ባለሥልጣን ማመልከት አለበት ብለዋል።

# ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት ለስራ እድል ፈጠራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመግታት ወጣቶችን ብቁ በማድረግ በክህሎት እና ሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየሰተራ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል ገለጹ።

ኢትዮጵያ በሊቀመንበርነት የምትመራውና 11 ሀገራት የሚገኙበት የምስራቅ አፍሪካና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ቀጠናዊ የሚኒስትሮች ፎረም "ቀጠናዊ የክህሎትና የወጣቶች ሥራ ስምሪት" በሚል በአዲስ አበባ እየተካሄደ ይገኛል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ በቀጠናው ሀገራት ክፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት በመኖሩ በቀጠናው ሀገራት መካከል ይህንን ውይይት ማድረግ የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ለውጦችን ያመጣል።

የሰዎች ዝውውርን ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትሎ እንዲከናወን መነሻና መተላለፊያ የሆኑ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በቀጠናው ሀገራት መካከል ወጥ የሆነ አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል። ለዚህም ለወጣቶች የሥልጠናና ሥራ ፈጠራ ተግባራት አስፈላጊ የሆነውን የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት ወጥ ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ኬንያ ላይ በተደረገው ውይይት የወጣቶችን ክህሎት በማዳበር ማብቃትና ሥራ ዕድል መፍጠር ላይ ካልተሠራ ኢ- መደበኛ የሰዎች ዝውውርን ተከትለው የሚመጡ ችግሮችን ማስቆም አይቻልም የሚል ሃሳብ በማምጣቷ እዚህ ላይ የሚሰራ የሙያተኞች ቡድን እንዲቋቋም ተወስኗል።

የሰዎች ዝውውርን ለመቀነስ ከፖሊሲ ጀምሮ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎችን በማሻሻል እየሰራች እንደምትገኝም የገለጹት ሚኒስትሯ፤ በዚህም የተለያዩ ስምምነቶችን በመፈራረም ዓለምአቀፍ ልምዶችንም በመጋራት እና



**ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል**

ፎረሙንም በመምራት ላይ ትገኛለች ብለዋል።

በውይይቱ መክፈቻ ላይ የዓለምአቀፉ ፍልሰተኞች ድርጅት የኢትዮጵያ ተወካይ አቢባቱ ዋኔ እና የቀጠናው ዳይሬክተር ተወካይ ባስተላለፉት መልዕክት፣ በቀጠናው የሚገኙ ወጣቶችን ብቁና ተወዳዳሪ ለማድረግ የሥራ ዕድል እንዲስፋፋ ሀገራት በትብብር እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ብለዋል።

ምክረ ሃሳቦችን የሚያቀርበው ቡድኑ ምርጥ ተሞክሮዎችን በማለዋወጥ በጋራ እንደሚሰራም ተጠቅሷል።

# በ2015 የተማሪዎችን ውጤታማነት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እንደሚገባቸው፣ እንዲሁም አዲስ የሚጀመሩ ትምህርቶች በምን መልኩ መከታተል እንደሚገባ ቅድመ ገለጻ መደረጉን ነግረውናል።

ለ9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች በሙከራ ደረጃ አዲስ የተካተቱ የትምህርት ዓይነቶች ኢኮኖሚክስ፣ ፐርፎርሚንግ ቪዧል አርትስ፣ የውጭ ቋንቋ መሆናቸውን ጠቁመዋል። የሥነዜጋ እነ የሥነምግባር ትምህርት ይባል የነበረው አሁን የዜግነት ትምህርት በሚል ተስተካክሎ የመጣ መሆኑን ገልጸዋል። ከስም ለውጡ በተጨማሪም ሀገርን ከመውደድ፣ እና ባህሪ ላይ ከመስራት አኳያ ያሉ ይዘቶቹ በተሻለ መጠን የተካተተበት መሆኑንም ገልጸዋል።

ትምህርት ቤቱ የተለያየ እምነት ያላቸው፣ የተለያየ ቋንቋ የሚጠቀሙ፣ ከተለያየ ብሔር የመጡት ተማሪዎቹ እርስ በእርስ በመከባበር፣ በመተሳሰብ፣ መማር እንደሚኖርባቸው ግንዛቤ መስጠቱንም አመላክተዋል።

ተማሪዎች ከአዲሱ መርሃ ግብር ጋር ከአሁኑ በትኩረት እንዲዘጋጁ እንዳይፈሩ፣ ግራ እንዳይጋቡ፣ ቀለል ባለ ቋንቋ እና በተሻለ መንገድ መቅረቡን እና መምህራኖቹም እነሱን በሚመጥኑ ደረጃ የተደለደሉ ናቸው ብለዋል።

አዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ በትምህርት ቤቱ ተግባራዊ መደረጉ ለትምህርት ቤቱም ለተማሪው አዲስ መሆኑን የገለጹት መምህሩ፤ አዲሱን ፍኖተ ካርታ ከማስተዋወቅ ስራ ጀምሮ ሰፊ ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ በተማሪ ባህሪ ላይ እንዲሰራ ትምህርት ቤቶች ሰፊ ጥረት እያደረጉ ነው ያሉት አቶ ሙሉዓለም በውጭ ያለው ፍላጎት ወደ ትምህርት ቤት እንዳይመጣ ከማድረግ አኳያ በበር ላይ በዲጂታል ፍተሻ እየተደረገ ነውም ብለዋል።

አስረኛ ክፍል ፈተና በመቅረቱ የመዘናጋቶች አሉ ያሉት ተማሪዎች የፖለቲካ ማስፈጸሚያ እንዳይሆኑም በትምህርት ሕጉ እና በተማሪ ባህሪ ላይ ሁሉም አካላት የበኩሉን እንዲሰራም አሳስበዋል።

በኮከበ ፅበሃ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የኬሚስትሪ መምህር በላይነህ አሰፋ በበኩላቸው፣


**ተማሪ አርሴማ መንግሥቱ**


**አቶ ሀብታሙ ዱጉማ**

የ2014 የትምህርት አሰጣጥ በመገምገምና በወቅታዊ ሰላም እና ደህንነት ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ በ2015 በምን መልኩ መሰጠት እንደሚገባው ውይይት መደረጉንም ጠቁመዋል።

በ2015 የትምህርት ዘመን ካለምንም የዲሲፕሊን ግድፈት እና የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ በጋራ እንሰራለን ብለዋል። በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ 9ኛ እና 10 ክፍል መጽሐፍ እንደደረሳቸውና ለማስተማሩም ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በኮከበ ፅበሃ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ አርሴማ መንግሥቱ በበኩሏ፥ ከክረምት ወራቱ ቆይታ በኋላ ትምህርት እስኪጀመር በጉጉት መቆየቷንና እስኪነጋ መቸኮሏን ገልጻለች።

አምና የነበራትን ውጤት ለማሻሻል በማቀድ የዘንድሮውን ትምህርት መዘመን የተሻለ ውጤት በማምጣት ትምህርት ቤቱንም ሀገርንም ለማስጠራት ማቀዷን ጠቅሳለች። ከዚህ ቀደም በፈተና ሰሞን ብቻ አጠና ነበር ያለችው ተማሪዋ አሁን ግን ከወዲሁ በእቅድ ለማጥናት መወሰኗን በመጠቆም ለሁሉም ተማሪዎች መልካም የትምህርት ዘመን እንዲሆን ምኞቷን ገልጻለች።

የእቴጌ መነን የልጃገረዶች አዳሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካዳሚክ ዘርፍ ምክትል ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ዱጉማ በበኩላቸው፣ ከባለፈው ሳምንት ጀምሮ


**መምህር በላይነህ አሰፋ**

ቅድመ ዝግጅት የተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ የመማር ማስተማሩን ትናንት መጀመሩን ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት በነበረው የኮቪድ ችግር አጀማመሩ ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩን አስታውሰው ዘንድሮ ግን ከትምህርት ሚኒስቴር በተሰጠው የትምህርት የቀን ቀመር መሰረት መጀመሩን ገልጸዋል።

የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መረጃ እንዳስታወቀው በትናንትናው እለት በአብዛኛው የሀገራችን አካባቢዎች የ2015 ዓ.ም ትምህርት ዘመን በደማቅ ሁኔታ ተጀምሯል። የትምህርት ዘመኑ የተሳካ እንዲሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡም ጥሪ ቀርቧል።

# ዘንድሮ የውጭ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ፌዴራል ፖሊስ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ቢሮ ጋር በመሆን አራት በተመረጡ ድንበር አካባቢዎች ማለትም በአፋር፣ ድሬዳዋ፣ ሶማሌ እና ሞያሌ በተደረገው ክትትል ወጪ ንግድ ሥርዓትን በተወሰነ መልኩ ማሻሻል ተችሏል ብለዋል።

እንደ አቶ ገመቹስ ገለጻ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለፈው በጀት ዓመት ከውጭ ንግድ 4 ነጥብ 63 ቢሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ አቅዶ 4 ነጥብ 12 ሚሊዮን ዶላር (89.06 %) መሰብሰብ ችሏል። ይህም ቀደም ሲል ከነበረው አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ500 ሚሊዮን ዶላር ልዩነት አሳይቷል።

ውጤቱ እንደዋዛ የተገኘ አለመሆኑን የጠቀሱት አቶ ገመቹስ፤ ሁሉም የሚመለከታቸው ሴክተሮች ትኩረት በመስጠት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በስሩ የሚገኙ አምራቾችን በመቆጣጠር የተገኘ ዉውጤት መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ገመቹስ ገለጻ፤ ወጪና ገቢ ንግዱን በአሰራር እና በአፈጻጸማቸው ሲታዩ በግብርና 72% ፣ ኢንዱስትሪ 12% ፣ ማዕድን 14% ነው።

በተዘረጉ አሰራሮች ውስጥ ግብርና በቡና፣ አበባ እና ጫትን ጨምሮ 105%፣ አልባሳት፣ ስጋ፣ ቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች እና መድሃኒት ዘርፍ 80%፣ በማዕድን በተለይ ታንታለምና ወርቅ 53% አፈጻጸም እንደነበራቸው ገልጸዋል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ትልቁ የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ማነቆዎች ከሕግ ማዕቀፎች ቀጥሎ በኮንትሮባንድ ንግዶች ምክንያት የሀገር ምርት ወደ ውጭ ሀገር መኮብለል እንደሆነም ጠቁመዋል።

የቁም እንስሳት በኮንትሮባንድ ከሀገር በማውጣት የጎረቤት ሀገራት ውጭ ምንዛሪ ገቢ በማገዝ ላይ እንደሚገኝ መንግሥት በመረዳቱ በድንበር አካባቢዎች በጥምረት ትኩረት ተሰጥቶበት እየተሰራበት ይገኛል ብለዋል።

የተጀመረው ስራ ጠቃሚ መሆኑ ከአፈጻጸሙ መረዳት እንደሚቻል ገልጸው ወደፊት ከጊዜ ወደ ጊዜ ግምገማ እና ክትትል እንደሚደረግበትም ጠቁመዋል።

ሕግ በማስከበር ረገድ የሚቀሩ ስራዎች ቢኖሩም በ2014 ዓ.ም የተጀመሩ ስራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል የውጭ ምንዛሪ ገቢን በማሳደግ ሀገርን ከውጭ ምንዛሪ ጫና ለማላቀቅ እየተሰራ እንደሆነም አቶ ገመቹስ ተናግረዋል።

# ሶስተኛ ዙር የውሃ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የመሳሰሉና የተለያዩ እውነትነት የሌላቸው ትርክቶች በግድቡ ሶስተኛ ዙር ሙሌት ሃሰትነቱ ተረጋግጧል። በመሆኑም ይህ በራሱ የውሃ መያዝ አለመያዝ አጀንዳቸውን ሊያስቀር የሚችል ነው።

የግድቡ ሙሌት ግንባታው እንዳይከናወን ከሚከላከሉ ኃይሎች አጀንዳ ማሳጣት በተጨማሪ የኢትዮጵያን የመደራደር አቅም ያሳድጋል ብለዋል ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ።

የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያ የተናገረችውን መፈፀም የምትችል ሀገር መሆኗን ያሳየችበት ታላቅ ፕሮጀክት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ የግድቡ ሶስተኛ ዙር ሙሌት መጠናቀቅ የኢትዮጵያን የመደራደር አቅም አሳድጓል የሚባለው በብዙ ምክንያቶች መሆኑን አንስተዋል።

ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት የኃይል ሽያጭ ማቅረብ መቻሏ አንዱ የመደራደር አቅሟን ከፍ የሚያደርገው መሆኑን ጠቁመዋል።

ሌላው የመደራደር አቅምን የሚጨምረው ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል በለማ ቁጥር ብዙ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሀገር ውስጥ መሳብ መቻል መሆኑን አንስተው፤ ከተለያዩ ሀገራት ብዙ ባለሀብቶች ወደ ሀገሪቱ የሚመጡ በመሆኑ ይህ በኢኮኖሚ ትርጉም ያለው ለውጥ ከመፍጠሩም ባሻገር የሀገሪቱን ተሰሚነት ይጨምራል ሲሉም ተናግረዋል።

በተለይ ግድቡ አረንጓዴ የኢነርጂ ምንጭ መሆኑ በጎረቤትና በቀጠናው የተፈጠረውን የመደራደር አቅም መጨመር እና ተፅዕኖ ወደ ዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት ከፍ የሚያደርግ መሆኑን አክለው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያውያን ግድቡ ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ከፍተኛ ርብርብ ማድረጋቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ በግድቡ ዙሪያ ያለፈው ታሪካችን ሲታይ የዓባይ ግድብ እዚህ ደረጃ ይደርሳል ብሎ ማሰብ እንደ ቅዠት የሚቆጠር ነበር ሲሉ አብራርተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሰብዓዊ መብት ስም ፖለቲካዊ ዓላማን ከማራመድ የበለጠ ኢሰብዓዊ ተግባር የለም!

ዓለማችን ለሴራ ፖለቲካ አዲስ አይደለችም፤ በየዘመኑ አገራትና ቡድኖች አለኝ የሚሉትን ያልተገባ ጥቅም ለማስጠበቅ ሴራን ዋነኛ እስትራቴጂ አድርገው ተንቀሳቅሰቀዋል። በዚህም ዓለማችን በተለይም የአፍሪካ አገራት ብዙ ዋጋ እንዲከፍሉ ተገደዋል። ዛሬም ቢሆን ይህ እውነታ ለአገራቱ ፈተና እንደሆነ ቀጥሏል።

ከቅኝ ግዛት መስፋፋት ዋዜማ ጀምሮ፣ በቅኝ ግዛት ዘመን፤ ከዚያም አልፎ በነጻነት ትግሉ ወቅትና ከነጻነት ማግስት ጀምሮ አፍሪካውያን ራሳቸውን እንዳይሆኑና ራሳቸው ያለሟቸውን የተሻሉ ህልሞች እውን አድርገው ወዳሰቧቸው ነገዎች እንዳይደርሱ በብዙ የሴራ ፖለቲካ ተጠላልፈው የግጭትና የድህነት ትርክት ማድመቂያ ሆነዋል።

ይህንን እውነታ ለመቀየር የሞከሩ አፍሪካውያን እና መሪዎቻቸው በየዘመኑ ብዙም እርምጃ ሳይራመዱ በአጭሩ ተቀጭተዋል። ለዚህም ስም ማጥፋትን ጀምሮ የውሸት /የፈጠራ / ትርክቶች ለጥፋት ተልእኮው ትልቅ ድርሻ ነበራቸው። እነዚህን ሴራዎች በመፍጠርም ሆነ በማሰራጨቱ ሂደት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የመገናኛ ብዙሃን አስተዋጽኦም የላቀ ነበር።

በእኛም አገር ያለው አሁናዊ ተጨባጭ እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም። አሸባሪው ትህነግ በህዝባዊ እንቢተኝነት ከስልጣን ከተወገደ ማግስት ጀምሮ፤ ለውጡ እና የለውጡ ኃይል ይዞት የተነሳውን ከፍ ያለ የፖለቲካ አስተሳሰብና ራዕይ ለማጨናገፍ የተለያዩ የስም ማጥፋትና የውሸት ትርክት ሴራዎች በአገር ውስጥ ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያስተናገድን እንገኛለን።

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የአሸባሪው ትህነግ በስልጣን መቆየት የጥቅም ምንጭ የሆናቸው ኃይሎች፤ የቡድኑን የስልጣን እድሜ ለማራዘም ያስችላሉ ያሏቸውን ተግባራት ሲፈጽሙ ታይተዋል። በዚህም የመንግስትን ስም ከማጥፋት ጀምሮ የውሸት ትርክቶችን በመፍጠር በመንግስት ላይ ጫና ለመፍጠር ብዙ ጥረዋል።

አሸባሪው ትህነግ በሰሜን ዕዝ ላይ በክህደት የፈጸመው ጥቃት መቀልበሱን ተከትሎ ራሱን ለማትረፍ ቡድኑ የፈጠረው ረሀብን የጦር መሳሪያ አድርጎ የመጠቀም የውሸት ክስ በቡድኑ ተቀጣሪ አክቲቪስቶች፣ ሎቢስቶች እና የቡድኑ የፕሮፓጋንዳ ማሽነሪዎች በስፋት አጀንዳ ሆነው ተናፍሰዋል።

ይህ ቡድኑ ህልውናውን ለማስቀጠል እንደ አንድ እስትራቴጂ የተጠቀመበት ሴራ የታሰበውን ውጤት ሳያመጣ፤ በተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በጋራ በካሄዱት ደረጃውን የጠበቀ ጥናት ከእውነት የራቀ መሆኑ ተረጋግጧል። ከክሱ በስተጀርባ የነበረውም ሴራ ከሽፏል።

በሪፖርቱም በጦርነት ወቅት ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ጥፋቶች በዘለለ በታቀደ መልኩ የተከናወነ የዘር ማጥፋትም ሆነ ረሀብን የጦር መሳሪያ አድርጎ የመጠቀም ሁኔታ እንዳልታየ በተጨባጭ መረጃና ማስረጃ ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ይፋ ሆኗል።

የሪፖርቱን ውጤት በከፊል የተቀበለው መንግስትም በሪፖርቱ የቀረቡና መስተካከል አለባቸው የተባሉ ጉዳዮችን ወደ ማስተካከል ገብቷል። የወሰዳቸውንም የማስተካከያ እርምጃዎች ይፋ አድርጎ፤ ለትግራይ ሕዝብ ያለውን አጋርነት በተግባር አሳይቷል። ይህም ተግባሩ በአብዛኛው የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ እውቅና አትርፎለታል።

በተጻራሪው አሸባሪው ትህነግ የጋራ ሪፖርቱ በሱና በጥቅም አጋሮቹ የተገመወደውን ሴራ ማክሸፉን ሲመለከቱ ፤ ሪፖርቱን ሙሉ በሙሉ አለመቀበሉን በመግለጽ፤ ገለልተኛ ለሆኑት ዓለም አቀፍና አገራዊ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽኖች ያለውን ንቀት በአደባባይ ገልጿል።

ይህ በዚህ ሁኔታ ባለበትና አሻባሪው ትህነግ ተጨማሪ ሁለት ጦርነቶችን በአገር ላይ አውጆ ከፍ ያለ ውድመት ባደረሰበትና እያደረሰ ባለበት፤ በውጤቱም እንደቀደመው ጊዜ እንዳሰበው ሳይሆንለት ሲቀር፤ ለቀደመው ጩኸቱ ዳግም ሕይወት በመስጠት ከተለያዩ አካላት ጋር እየሰራ ይገኛል።

ሰሞኑን ከኢፕድ ታማኝ ምንጮች እንደተገኘው መረጃ ራሱን በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ ኮሚሽን ስም የሰየመ ተቋም በአገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተካሂዷል በሚል አዲስ ሪፖርት ለማውጣት እየተዘጋጀ መሆኑ ይፋ ተደርጓል።

ራሱን በዓለም አቀፍ ኮሚሽን ስም የሰየመው ይህ አካል ቀደም ሲል ምርመራ የተደረገበትን ጉዳይ ዳግም ለመመርመር ለምን ተነሳ፤ አሸባሪው ትህነግ ለሶስተኛ ጊዜ የለኮሰውን ጦርነት ለመቀልበስ መንግስት የመከላከል እርምጃ እየወሰደ ባለበት እና ቡድኑ ለህልውናው ለአጋሮቹ የድረሱልኝ ጥሪ እያሰማ ባለበት ወቅት ሪፖርቱን ይፋ ማድረግ ለምን አስፈለገው ? የሚሉት ጥያቄዎች ለብዙዎች እንቆቅልሽ ሆነዋል።

ታማኝ ምንጮቹ እንዳመለከቱት፤ ሪፖርቱ ህዝባዊነቱንና ህገመንግስታዊ ኃላፊነቱን በብዙ መስዋእትነት በመወጣት ላይ የሚገኘውን የአገሪቱን የመከላከያ ሰራዊት በማጠልሸት ላይ ነው ያተኮረው፤ ከዚያም ባለፈ የትግራይ ሕዝብ በግጭቱ ወቅት የምግብ አቅርቦት እንዳያጋጥመው ብዙ ዋጋ እየከፈለ ባለው መንግስት ላይ ዓለም አቀፍ ጫና በመፍጠር ለቡድኑ ትንፋሽ ለማሰባሰብ የተዘጋጀ ነው።

ሊወጣ ያለው ሪፖርት በመረጃ አሰባሰቡ፤ ትንታኔ ሆነ ሪፖርት አቀራረቡ ዝቅተኛ የሚባለውን መመዘኛ እንኳን ማሟላት ያልቻለ፤ ከተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እውቅናና ድጋፍ ያልተሰጠው፤ ችግር አለ ከተባለበት ቦታ እጅግ ርቆ በስልክና በስማ በለው የተሰራና አድሏዊነት በስፋት የተንጸባረቀበት በአጠቃላይ ግልጽነት የጎደለውና ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ ምንጮቹ አረጋግጠዋል።

ይህ የተቋሙ የተሳሳተ መንገድ በየትኛውም ሁኔታ የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ የማይችል ከመሆኑም በላይ፤ የተቋሙን ማማሟቅ ተከትሎ የአሻባሪው ትህነግ ተቀጣሪ አክቲቪስቶች፣ ሎቢስቶች እና የቡድኑ የፕሮፓጋንዳ ማሽነሪዎች የጀመሩት ጩኸት ሴራውን ብቻ ሳይሆን ሴራውን የቱን ያህል ተናበው ለመከወን የተልእኮ አንድነት እንደፈጠሩ ጭምር ያሳየ ነው።

መንግስት ከማንም ይልቅ በዜጎቹ ጉዳይ ከሱ የበለጠ ሊያስብ የሚችል አለ የሚል እምነት የለውም። እያንዳንዱ ተግባራዊ እንቅስቃሴውም ከዚሁ አውነታ የመነጨ፤ ለዚሁ እውነታ የተገዛ ነው። በዜጎች ስም የሚደረጉ የሴራ ጉንጓኖዎችንም በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም፤ ወደፊትም አይሆንም። በአጠቃላይ በሰብዓዊ መብት ስም ፖለቲካዊ ዓላማ ከማራመድ የበለጠ ኢሰብዓዊነት አለመኖሩም ሊሰመርበት ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# የትግራይ ዲያስፖራ አሰላለፉን ያስተካክል

(አቤል ገ/ኪዳን)

ሰሞኑን የአሸባሪው ትህነግ አመራሮች ለሶስተኛ ጊዜ በለኮሱት ጦርነት ስጋት ውስጥ ገብተው ሊታይ የሚችል መረበሽ ውስጥ ገብተዋል። ነገሮች ውስብስብ ሆነውባቸዋል። ከቡድኑ በላይ በዚህ ሁኔታ እየታወከ ያለ ሌላ አካልም አለ። እሱም የትግራይ ዲያስፖራ ነው። ይህ ኃይል በዚህ ጦርነት ውስጥ ያለው ድርሻ ቀላል የሚባል አይደለም።

አሸባሪው ትህነግን በፋይናንስም፤ በዲፕሎማሲም፤ በሞራልም የሚደግፍ ኃይል ነው። ይህ ኃይል የቡድኑ የጀርባ አጥንቱ ስለሆነ እንዲከፋው አይፈልግም። ለዚህም ነው መሬት ላይ ምንም ቢፈጠር የቡድኑ አመራሮች በቴሌቪዥን ብቅ እያሉ ድል እየተገኘ እንደሆነ እና ዲያስፖራው ድጋፉን መቀጠል እንዳለበት ጥሪ የሚያቀርቡት።

ዲያስፖራውም በዚህ ተደስቶ አሁንም ዶላር ሰብስቦ ይልካል፤ ሰልፍ ወጥቶ ይንከባለላል ወዘተ...። ሰሞኑን እንደውም በታደሰ ወረደ የሽንፈት መግለጫ በጣም በተደናገጠበት ወቅት ጌታቸው ረዳ እሱን እንዲያስተባብል ተልኮ ነበር። በሰጠው መግለጫ ላይም ይህ መረጋጋት እና ስክነት የጠፋበት ኃይል እንዲረጋጋ ተማጽኗል።

“አሁንም እደጋግመዋለሁ፤ አገር ውስጥ ሆነ ውጭ ያላችሁ፣ አገር ውስጥ ያላችሁ ህዝባችን በደጀንነት እየሰራችሁ ነው ውጭ ያላችሁም እየሰራችሁ ነው። በተለይ ግን ውጭ የምትኖሩ ባሉሽ አሉሽ ተባራሪ ወሬዎች በቀላሉ መረበሽ ብዙ አይጠቅመንም።” ብሏል ጌታቸው። እንዲረጋጋመ የተወሰኑ የውሸት የድል ዜናዎች ለግሶታል።

አንዳንዴ እነ ጌታቸው ለዲያስፖራ ደጋፊያቸው የሚዋሹለት ውሸት በጣም አስደናቂ ቢሆንም ይህ ኃይል ግን አንዴ በጦርነት ሰክሯልና እውነቱን እና ውሸቱን ለመለየት ሲቸገር ይስተዋላል። ለምሳሌ ያህል ሰሞኑን በተደረጉ ጦርነቶች 90ሺ ወታደር ገድለናል ብሎ ጌታቸው ሲናገር ውሸትህን ነው ያለው የለም።

እንዲያውም በቃ እያሸነፍን ነው ብለው ተደስተው ነበር። ጌታቸው ይህ ጦርነት ከተጀመረ በኋላ ገደልን ያለው ወታደር ቁጥር ቢደመር ኢትዮጵያ ካላት ሰራዊት ቁጥር በብዙ እጥፍ የበለጠ እንደሆነ እና ይህን ያህል ሰራዊት መደምሰስ ከተቻለ ጦርነቱ ከብዙ ጊዜ በፊት ያልቅ እንደነበር ማገናዘብ ግን አልተቻላቸውም።

የሆነ ሆኖ ይህ ኃይል አሁን ወደ ቀልቡ እንዲመለስ የሚያደርግ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ትግራይ ውስጥ ያለው ህዝብ ጦርነት እንደበቃው እና እየተዋጋ ያለው በግድ ከጀርባው መሳሪያ ተደግኖበት እንደሆነ በጦርነቱ ከተማረኩትም እዚያው ትግራይ ውስጥ ካሉትም በተደጋጋሚ ተሰምቷል።

የመዋጋት ሞራሉም አላማውም አሁን ያለው በአንዳች ተአምር ይህን ጦርነት አሸንፈው ከተጠያቂነት መዳን በሚመኙት የትህነግ መሪዎች እና እውነታቸውን አልቀበልም ብሎ ቀን ከሌሊት በሚዳክረው የትግራይ ዲያስፖራ ውስጥ ብቻ ነው።

የቡድኑን መሪዎችን ጦርነትን እንዲያቆሙ ማሳመን መተንፈስ እንዲያቆሙ የማሳመን ያህል ከባድ ነውና አይሞከርም። ጦርነት የህልውናቸው መሰረት ነው። ዲያስፖራው ግን በምን ምክንያት በዚህ እሳት ላይ ጋዝ ማርከፍከፉ እንዳስደሰተው አይታወቅም። በምንም ምክንያት ቢሆን ግን ከዚህ ተግባሩ እንዲታቀብ ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ይህ ጦርነት በቀጠለ ቁጥር ሚኞቹ የእሱ ዘመዶች ናቸውና ነው።

ብዙዎቹ ዲያስፖራዎች (ቴዎድሮስ አድሀኖምን ጨምሮ) ትግራይ ውስጥ ስልክ ስለማይሰራ ቤተሰቦቻቸውን ማግኘት እንዳልቻሉ፤ የባንክ ኔትወርክም ስለሌለ ገንዘብ መላክ እንዳልቻሉ እና ቤተሰቦቻቸው በዚህ እየተጎዱ እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን ዘወር ብለው ደግሞ በማህበራዊ ሚዲያ ገጻቸው ቡድኑ የሚያሞካሽ እና በርታ የሚል ቅስቀሳ ያደርጋሉ፤ ይህን ለሚያደርጉ ሚዲያዎች ገንዘብ ይለግሳሉ።

በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለሚያሳድሩ የምዕራቡ ፖለቲከኞች መደለያ ገንዘብ ይከፍላሉ። ለትህነግ እና መሰሎቹ መሳሪያ መግዣ ገንዘብ ያዋጣሉ። ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው ኢትዮጵያን ሲራገሙ ይውላሉ። ሌላም ሌላም ያደርጋሉ። በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ለመሆን አይቸገሩም። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ሰላም እንደምን ሊመጣ ይችላል?

የትግራይ ዲያስፖራ በዚህ ጦርነት ላይ ጦርነቱን ከማቀጣጠል ያለፈ ፋይዳ አልነበረውም። አሳዛኙ ነገር ደግሞ እነሱ የሚያርከፈክፉት ነዳጅ ያቃጠለው የራሳቸውን ቤት የራሳቸውን የስጋ ዘመዶች ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ ይህ ባይሆን መልካም ነበር። አሁንም ግን አንድ ሌላ እድል ይኖራል። ይህ እድልም ዲያስፖራው ወገንተኝነቱን ከትህነግ አንስቶ ለትግራይ ህዝብ ብቻ ማድረግ።

ለትግራይ ህዝብ ወገንተኛ ከሆኑ አሁን ላይ የትግራይ ህዝብ ምን እንደሚፈልግ ያውቃሉ። ያን ካወቁም ተሳትፎቸውን በዚያው ልክ ያስተካክላሉ። የትግራይ ህዝብ ወቅታዊ ፍላጎት ሰላም ነው። ጦርነቱ እንዲቆም፤ መብራት እና ኔትወርክ አገልግሎት እንዲቀጥል፤ መንገዶች እንዲከፈቱ፤ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለሱ፤ ገበሬው ወደ እርሻው እንዲሰማራ ነው ፍላጎቱ። ይህ ፍላጎት ከትህነግ ፍላጎት ጋር ፈጽሞ አይገናኝም።

የአሸባሪው ትህነግ ፍላጎት በማንኛውም መንገድ ከተጠያቂነት መዳን ከተቻለም ስልጣን ይዞ መቀጠል በዋነኝነት ደግሞ እንደ ንጉሳዊ ቤተሰብ እነሱ እና የእነሱ ደቀ መዛሙርት ብቻ እድሜ ልካቸውን የሚመሯት ነጻ አገር ትግራይን ገንጥሎ መመስረት ነው። ይህ የቡድኑ ህልም ከትግራይ ህዝብ ፍላጎት ጋር ፈጽሞ ሊገጥም አይችልም።

ቡድኑ ከተፈጠረበት እለት ጀምሮ የትግራይ ህዝብ ከጦርነት አርፎ አያውቅምና ነው። ያለፉትን 47 አመታት ታሪክ አገናዝበን አንድ ነገር በእርግጠኝነት መናገር የምንችለው ከአሁን በኋላ የትግራይ ህዝብ በትህነግ አመራር ውስጥ ሆኖ ከሌላ አዲስ ጦርነት ውጭ ሊያገኝ የሚችለው አንዳች በጎ ነገር እንደሌለ ነው።

ስለዚህም ምርጫው ግልጽ ነው። የትግራይ ህዝብ በተለይም የትግራይ ዲያስፖራ ከአሁን በኋላ አሰላለፉን ሊያስተካክል እና እየሰመጠች ካለቸው የአሸባሪው ትህነግ መርከብ ዘልሎ ሊወርድ ይገባል። አሰላለፉን ከትግራይ ህዝብ ጋር አድርጎ ወደ ጦርነት አትማግዱን፤ መሳሪያ አውርዱና ሰላም ስጡን ሊል ይገባል። አልያም ግን አሁንም በዚሁ በያዘው ጦርነቱን የማቀጣጠል እና ቡድኑን የመደገፍ መንገድ ከቀጠለ መጨረሻው የከፋ ሀዘን እንደሚሆን በቅርብ ጊዜ ያያል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# አገሬ ለኔ ምን አደረገችልኝ ከማለት፤ ለአገሬ ምን አደረኩኝ ለሚለው ጥያቄ ቅርብ እንሁን

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

እንደ አሜሪካ ያሉ አንዳንድ ሀያላን አገራት ዘመን የተሻገረ የስኬት ሚስጥር አላቸው..እርሱም ከላይ ለርዕሴ የተጠቀምኩት አባባል ነው። ዛሬም ድረስ አሜሪካና አሜሪካውያን በዚህ ‹አገሬ ለኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለአገሬ ምን አደረኩት› በሚል እሳቤ ውስጥ ናቸው። አሜሪካውያን እንዴት አደጉ? እንዴት ሰለጠኑ? እንዴትስ ይሄን ልዕልና አገኙ? ብሎ ለጠየቀ መልሱ ይኸው ነው ።

አእምሮና ልብን የሚያነሳሱ። አንዳንድ አንደበቶች ፈዋሽ ናቸው። ተደምጠው የሚያበቁ ብቻ ሳይሆኑ በሰሚ ልብ ውስጥ ዘላለማዊ ህይወት የሚዘሩ፤ አንዳንድ ጥያቄዎች ተራ መስለው ከብዙ መከራና እንግልት የሚያወጡ ሆነው እናገኛቸዋለን። አሜሪካውያን ከምንምነት የወጡት በዚሁ በወቅቱ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት ጆሴፍ ኬኔዲ አገር አቀፍ ፍልስፍና ነበር።

አንዳንድ ጥያቄዎች አገር ይፈጥራሉ። አንዳንድ ጥያቄዎች ደግሞ አገር ይሰውራሉ። ቃላትን በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው ተዐምር የመፍጠር አቅም አላቸው። እድገትና ስልጣኔ በምኞት ብቻ የሚመጡ ነገሮች አይደሉም። ህልሞቻችን እውነትነትን እንዲያገኙ አነቃቂና አበረታች ሀሳብና አንደበቶች ይሻሉ። ብዙዎቻችን ጠባቂዎች በሆኑበት፤ ከጠባቂነትም በላይ የምንፈልጋቸው ነገሮች ደጃችን ላይ እንዲሆኑ የምንጠብቅ በሆንበት አገር ውስጥ፤ ብዙዎቻችን ተምረንም ሆነ ተመርቀን የመንግስትን እጅ በምንጠብቅበት አገር ውስጥ ነገዎቻችን ብሩህ ናቸው ብሎ መጠበቅ የዋሕነት ነው።

በመጠበቅ ውስጥ ለውጥ የለም። በመጠበቅ ውስጥ የሚፈጠር እድል የለም። እድሎቻችን ያሉት ዛሬን በመጠቀም ውስጥ ነው። ኢትዮጵያ አገራችን በየአመቱ ከሁለት መቶ ሀምሳ ሺ ተማሪ በላይ አዲስ ስራ ፈላጊ ተመሪዎችን ታስመርቃለች። ያለው ስራ ሳያገኝ..ተመርቆ ቁጭ ያለው እንጀራ ፍለጋ መንግስትንና አገሩን በሚጠብቅበት ሁኔታ ላይ ሌላ ስራ ፈላጊ መጨመሩ ሁኔታውን ምን ያክል አስቸጋሪ እንደሚያደርገው መገመት አይከብድም።

ከተማረውም ሆነ እየተማረ ካለው የሚጠበቀው መንግስትን ሳይጠብቅ በተማረው ትምህርት ለራሱም ሆነ ለሌሎች እድሎችን መፍጠር ነው። በመጠበቅ ውስጥ ልዕልና የለም። ለምሳሌ ተመርቆ ስራ በመፈለግ ሶስት አመት ያሳለፈ አንድ ተማሪ ከመጠበቅ ወጥቶ እነዛን በስራ መፈለግ የባከኑ ሶስት አመታቶች ስራ ፈጥሮ ቢሰራባቸውና ራሱን ለመለወጥ ቢጠቀምባቸው ዛሬ ላይ ተመርቀው ስራ ላጡ ተማሪዎች እንጀራ መሆን ይችል ነበር።

ሁለትና ሶስት ዓመት ስራ ፍለጋ ስንባዝን ምንም የማይመስለን ስራ በማጣታችን እንቆጫለን። ስራ እየሰሩ ስራ መፈለግ እኮ ይቻላል። ህልምና ራዕይን እየኖሩ የተሻለ ነገር መጠበቅ እኮ ይቻላል። እኛ ግን ጋዋናችንን ባወለቅን ማግስት መንግስት ስራ ፈልጎ እንዲሰጠን እጃችንን አጣጥፈን የምንቀመጥ ነን። አንዳንዶች ጭራሽ ለመንግስት ብለው የተማሩ የሚመስላቸው አሉ..መንግስት ቤታቸው ድረስ መጥቶ ካልቀጠራቸው በአገራቸው ላይ ለንቦጫቸውን የሚጥሉ።

ከመጠበቅ እስካልወጣን ድረስ ከፍ ማለት አንችልም። ከመጠበቅ እስካልተላቀቅን ድረስ ራሳችንን የምንለውጥበት አንድም አጋጣሚ አይገኝም። አገሬ ምን አደረገችልኝ? ከሚል አመለካከት ወጥተን እኔ ለአገሬ ምን አደረጉላት? እስካላልን ድረስ የህልሞቻችንን ጥግ አንደርስበትም። ድህና በብዙ ማጣት ውስጥ ያለች አገር ዜጎቿን እንደፍቃዳቸው ማስተናገድ አትችልም። አሁን ባለው ኢኮኖሚ፣ አሁን ባለው ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ መንግስት ፍላጎቶቻችንን ማሟላት አይችልም።

ራሳችንን የምንለውጠው ራሳችን ነን። እኛ ከመጠበቅ እስካልወጣን ድረስ ሊለውጠን የሚችል ኃይል ምድር ላይ የለም። የዓለም ስልጣኔ የግለሰቦች ስልጣኔ ነው። ግለሰብ ሲሰለጥንና ሲለወጥ ነው አገርና ማህበረሰብ የሚለወጠው። በራሳችን ውስጥ ራሳችንን ገለንና አኮስሰን መንግስት ካለወጠኝ የምንል ከሆነ በጊዜ ከፈናችንን ብንገዛ ይሻለናል። ዓለም በግለሰቦች ለውጥ ውስጥ ናት..እየተራመደች ያለችውም በጥቂት ሀሳባውያን እምነት ውስጥ ነው።

ጆሴፍ ኬኔዲ አሜሪካንን ለመለወጥ ሲነሳ መጀመሪያ ከራሱ ነበር የጀመረው። ፕሬዚዳንት ሆኖ ኋይት ሀውስ ሲገባ በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ለዘላለም የሚታወስ አንድ በጎ ነገር መስራት አለብኝ ብሎ ነበር። እንዳሰበውም ለሁላችንም ቀላል በሚመስል ግን ደግሞ በአይደለ ንግግር ‹አገሬ ለኔ ምን አደረገችልኝ ሳይሆን እኔ ለአገሬ ምን አደረኩላት› በሚል ፍልስፍና አገሩን ወደፊት ማራመድ ቻለ። አሁን ላይ መላው አሜሪካውያን ለአገራቸው የሚለፉ ናቸው። ዓለም ላይ ራሳቸውንም ሆነ አገራቸውን ከሚወዱ ጥቂት አገራት ውስጥ አሜሪካውያን ተጠቃሽ ናቸው።

ራስን ለመቀየር መጀመሪያ አስተሳሰብን መቀየር ያስፈልጋል። አገር ለመቀየር መጀመሪያ ራስን መቀየር ግድ ይላል። የጠፋን እውነት ይሄ ነው። ተመርቀን መንግስትን የምንጠብቅ ከሆነ፣ ምንም ነገር ኮሽ ባለ ቁጥር መንግስትን የምንጠራ ከሆነ፣ በአካባቢያችን ላለ ረብሻ፣ ላለ ቆሻሻ፣ ላለ የውሀ ቱቦ፣ ላለ ኮረኮንች መንገድ መንግስትን ተጠያቂ የምናደርግ ከሆነ ገና አስተሳሰባችንን አልቀየርንም ማለት ነው።

በገቡን ጥቂት እውነቶች ላይ ተረማምደን ያልገቡንን እልፍ እውነቶች ሀሰት ናቸው ማለት የለብንም። አገራችን የምሰጠን ምንም የላትም። ከሰጠችንም እኛ የሰጠናትን ነው፤ ካልሰጠናት የምሰጠን አንዳች የላትም። እንድሰጠን ልንሰጣት ይገባል። ተመርቀን ስራ እንድናገኝ በተመረቅንበት የሙያ ዘርፍ በተዐማኝነት ልናገለግላት ይገባል። ወልደን እንድንስምባት፣ ዘርተን እንድንቅምባት ፍቅርና ትህትናን የሚያውቁ ዜጎች ልንሆን ይገባል።

አገራችን እንድትሞላ ከራሳችን ላይ የምናጎለው እውነት ያስፈልጋል። ትውልዱ እንዲባረክ ጥላቻን ያስቀደመ ልብ ሳይሆን ለይቅርታ የበረታ ሰውነት ያስፈልገናል። ለምንም ነገር አገር እየጠበቅን፣ ለምንም ነገር አገራችንን ሰበብ እያደረግን የምንሞላው ባዶነት የለም። መጀመሪያ በውስጣችን ያለውን የጥላቻ ስፍራ፣ የመገፋፋት ባዶነት እንሙላ። እኛ ሳንሞላ የምትሞላ አገር የለችንም። እኛ ሳንለወጥ፣ እኛ ልክ ሳንሆን የምትለወጥና ልክ የምትሆን አገር አልተሰጠችንም።

አገር ማለት ከራሳችን ለራሳችን የምንሰጠው ክብር ማለት ነው። ትውልድ ማለት ከራሳችን ለራሳችን የምንቆርሰው እውነትና ማለት ነው። ክብራችንን አጉድለን፣ እውነታችንን አሳንሰን የምንወጣው የስኬት ተራራ የለም። የስኬት ተራራዎች በበረቱ እግሮች የሚወጡ ናቸው። የስኬት ከፍታዎች በማሰብና በትጋት የሚገፉ ናቸው። እግሮቻችንን አንድ ቦታ ላይ ተክለን መጠበቅ አስለምደናቸው የምንወጣው የስኬት ተራራ የለም።

መጀመሪያ ልማዶቻችንን እንቀይር። እንዳንቀሳቀስ፣ እንዳንበረታ ያደረጉንን አጉል እምነቶቻችንን እናጥፋ። ልማድ አደገኛ ነገር ነው.. አባቶቻችን ‹ከሰይጣን በላይ ልማድህን ፍራ› ይላሉ። ሰይጣን በስመ አብ ስትለው ይሄዳል ልማድ ግን ምንም ብንለው አይሸሽንም። የዛሬ የድህነት ምክንያቶቻችን በስመ መስቀል ያላባረርነው የአጉል ልማድ ውጤታችን ነው እላለው። የመጠበቅ ልማዳችንን፣ የጥላቻ ልማዳችንን፣ ያለመነጋገር ልማዳችንን፣ የተንኮል ልማዳችንን፣ እውቀትን ልህቀትን ያለመፈለግ ልማዳችንን፣ ሳይሰሩ የመብላት ልማዳችንን፣ ባጠቃላይ የእኩይ አስተሳሰብ ልማዳችንን መስበር ይኖርብናል።

ራስን ለመቀየር መጀመሪያ አስተሳሰብን መቀየር ያስፈልጋል። አገር ለመቀየር መጀመሪያ ራስን መቀየር ግድ ይሳል። የጠፋን እውነት ይሄ ነው

አገር፣ ህዝብ ታሪክ፣ ባህል፣ ወግ ስርዐት እውነት የሚሆኑት እኔ ለአገሬ ምን አደረኩላት? ብለን ራሳችንን ስንጠይቅ ነው። እስከዛሬ ባለመጠየቅ ውስጥ ነበርን። እስከዛሬ እውነት በሚመስል ውሸት ውስጥ ነበርን። እስከዛሬ ያልሰጠነውን ፍቅር፣ ያልሰጠነውን ክብር፣ ያልሰጠነውን እውነት ከአገራችን ስንጠብቅ ነበር። አገራችን እንድትሰጠን ልንሰጣት ይገባል። እናም ፍቅራችንን አንድነታችንን እንስጣት። ይቅርታን በጎነትን እንስጣት። እርቅን፣ ተነጋግሮ መግባባትን እናውርሳት። ይሄን ስናደርግ ነው የምሰጠን። ይሄን ስናደርግ ነው ፍላጎታችንን ለማሟላት አቅም የምታገኘው።

ተማሪ ከሆንን ችግሮቿን ሊቀርፍ በሚችል ብርታት ውስጥ እንሁን። ስራ ፈላጊ ከሆንን ከመጠበቅ ወጥተን ለጠባቂዎች አርዐያ እንሁን። በስራ ዓለም ላይ ከሆንን ደግሞ በእውነት ልናገለግላት ለራሳችን እንታመን ይሄን ስናደርግ የምትሰጠን ብዙ ነገር ይኖራታል። ያለዛ ግን ምንም የሌላትን እናታችንን ማስጨነቅ ነው የሚሆነው። ያለዛ ግን አንዳች የሌለው ድሀ ህዝብን መክዳት ነው የሚሆነው።

ከነበርንበት አስተሳሰብ ወጥተን ‹እኔ ለአገሬ ምን አደረኩላት? ወደሚል ተገቢ ጥያቄ እንመለስ። እስከዛሬ ጠይቀን ያልመለስነው ጥያቄ ይሄ ነው እላለው። በዚህ ጥያቄ ውስጥ ነው ለዘመናት ፈልገን ያጣነውን እውነት የምንደርስበት። በዚህ ጥያቄ ውስጥ ነው፤ ለዘመናት ተራምደን ያልደረስንበትን የእድገትና የስልጣኔ መልሶች የምናገኘው። ራሳችንን በማይጠቅመን እውነት ውስጥ ሸሽገን መኖራችን ይብቃን።

ከእንግዲህ አገሬ ለኔ ሳይሆን እኔ ለአገሬ ምን አደረኩ? ምን ሰራሁ? ምን ፈጠርኩ? ወደሚል እውነት ልንሸጋገር ይገባል። እንደ ዜጋ እንደ መንግስት እንደየትኛውም አገር ወዳድ ልቦች የጠፋችብንን ኢትዮጵያ፣ የጠፋብንን ስልጣኔ፣ የጠፋብንን አንድነት በዚህ ‹እኔ ለአገሬ ምን አደረኩ? በሚለው ጥያቄ ውስጥ ልንፈልገው ይገባል። ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደ ህይወት መርህ ልንመራበት የሚገባን ፍልስፍና ነው።

አንዳንድ ጊዜ ስልጣኔ በቀላል ቀመር የተቀመረ ጥበብ ነው። ቀመሩን አጠገባችን አስቀምጠን ሩቅ የምናይ፣ ለፍለጋ ሩቅ የምንሄድ ሞልተናል። አሜሪካውያን ሚስጥሩን ፍለጋ ሩቅ አልሄዱም..ሩቅ አላዩም ዛሬም ድረስ በዛ ሚስጥር ውስጥ ናቸው። ሚስጥሩ ራስን መጠየቅ ነው..ሚስጥሩ ወደሌሎች ጣትን ከመቀሰር ይልቅ እኔ ለአገሬ ምን አደረኩ? ለወገኔ ምን ሰራሁ? ብሎ ራስን መጠየቅ፤ ጠይቆም መልስ ማግኘት ነው።

ራሳችንን ከመጥቀም፣ ራሳችንን ከማገልገል፣ ብሄር እየለየን፣ ዘርና ጎሳ እየመረጥን ከመጮህ ወጥተን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን መሀል አድርገን ለጋራ ጥቅማችን ራሳችንን እናዘጋጅ። ተባብረን አገር ማሳደግ ያቃተን እኮ በአባቶቻችን የጋራ ሀሳብና ህልም የቆሙ ታሪኮቻችንን ተለያይተን ስላነበብናቸው ነው። በጋራ የተጻፉ ታሪኮች በጋራ ነው የሚነበቡት። በጋራ የተፈጠሩ እውነቶች በጋራ ነው የሚጸኑት። በአሁኑ ሰዐት ራሳችንንም ሆነ አገራችንን ልንለውጥበት የምንችልበት አንድ መንገድ ብቻ አለን እርሱም ‹እኔ ለአገሬ ምን አደረኩላት? በሚለው የተፈጠነ ጽንሰ ሀሳብ ነው። በዚህ እውነት ውስጥ እንብቀል..በዚህ እውነት ውስጥ ወጥተን እንግባ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የአፈር ምርመራን ፈጣንና ቀላል ያደረገው ቴክኖሎጂ

**አንተነህ ቸሬ**




**የአፈር መመርመሪያ መሳሪያው በአንድ አካባቢ ዘር ከመዘራቱ በፊት አፈሩ ለየትኛው የዘር ዓይነት ምቹ እንደሆነ በመለየት የምርት ውጤትን ከፍ ለማድረግ ያግዛል፤**

‹‹የቴክኖሎጂ ዘመን›› የሚባለው የአሁኑ ጊዜ፤ የረቀቀውን ሰው ሠራሽ የልኅቀት ቴክኖሎጂ (Artificial Intelligence) በመጠቀም የሰውን ኑሮ ቀላል ያደረጉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙበት ወቅት ነው። አገራትም መጭውን ጊዜ በማሰብ ቴክኖሎጂን እንደዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ በመያዝ ምጣኔ ሀብታቸውን በቴክኖሎጂ የሚታገዝ እንዲሆን ጥረት እያደረጉ ናቸው።

ከአስር ዓመቱ የኢትዮጵያ አገራዊ የልማት እቅድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች (Strategic Pillars) መካከል አንዱ የቴክኖሎጂ አቅምን በማሳደግ ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት ነው። ይህን ለማሳካት ደግሞ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ ወሳኝ ግብዓት እንደሆነ ይታወቃል። በተለይም የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማ ማድረግ ለሚችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የላቀ ትኩረት መስጠት አገራዊ የልማት እቅዱን ለማሳካት ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

በአሁኑ ወቅት በቴክኖሎጂ ማበልፀግ ላይ የተሰማሩ በርካታ ጀማሪ የቴክኖሎጂ ተቋማት (Startup Technology Companies) እየተቋቋሙና ማኅበረሰብ ተኮር የሆኑ የፈጠራ ውጤቶችን ለገበያ ለማቅረብ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ተቋማት መካከል ግብርናን በማዘመን ላይ አተኩረው የሚሰሩት ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም። የተቋማቱ የፈጠራ ውጤቶች ለማኅበረሰባዊ ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት ያለሙ ሲሆኑ፣ በረጅም ጊዜ ተግባሮቻቸው አጠቃላይ አገራዊ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴውን ወደ ዲጂታል አሰራር ያሻግራሉ ተብሎ ተስፋ የሚጣልባቸው ናቸው።

እንደ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (Artificial Intelligence)፣ ኔትወርኪንግ (Net working) እና የመረጃ ትንተና (Data Analysis) ያሉ ዘመን አፈራሽ ቴክኖሎጂዎችን ለማኅበረሰባዊ ችግሮች መፍቻ በማዋል ላይ አተኩሮ የሚሰራው ‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› የተሰኘው የቴክኖሎጂ ድርጅት ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ተቋማት መካከል ይጠቀሳል።

የ‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› ተባባሪ መስራችና ዋና ስራ አስኪያጅ ጃርሚያ ባይሳ እንደሚናገረው፣ ‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› በአሁኑ ወቅት በቴክኖሎጂው ዘርፍ ለዓለም እየተዋወቁና ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን (Emerging Technologies) ተጠቅሞ የኅብረተሰቡን ኑሮ ቀላል ለማድረግ የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚያበለጽግና የሚያቀርብ ተቋም ነው። በ2010 ዓ.ም የተመሰተረው ተቋሙ፣ በአሁኑ ወቅት በገበያ ላይ የሚገኙና ወደፊትም ወደ ገበያ ገብተውና ቆይተው ለኅብረተሰብ ችግሮች መፍትሄ የሚሆኑ፤ በግብርና፣ በጤና፣ በትራንስፖርት፣ በትምህርትና በሌሎች ዘርፎች አገልግሎት የሚሰጡ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ አተኩሮ ይሰራል። ቴክኖሎጂዎቹ አንዳንዶቹ ከሌሎች ጋር ተጣምረው የሚሰሩ ይሆናል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ለየብቻቸው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ ናቸው።

ተቋሙ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ የኅብረተሰቡን ችግሮች በእጅጉ የሚያቃልሉና የሚፈቱ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ይፋ አድርጓል። ለአብነት ያህል በግብርናው ዘርፍ ካበለፀጋቸው ፈጠራዎች መካከል የእፅዋትን በሽታ የሚለይ የቴክኖሎጂ ውጤት አንዱ ነው። ይህ ቴክኖሎጂ የእፅዋት በሽታዎችን ከመለየት በተጨማሪ የተለየውን በሽታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ምን መደረግ እንዳለበትም የሚጠቁም ነው። ቴክኖሎጂው አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሽልማቶችንም ማሸነፍ ችሏል።

የእንስሳትን በሽታ መለየት የሚችልና ጤንነታቸውን የሚከታተለው ‹‹ጃርሱማ›› የተሰኘው የፈጠራ ውጤትም የቴክኖሎጂ ተቋሙ የሥራ ውጤት ነው።

የሲቲ ስካን (CT Scan) ምስሎችን ተቀብሎ የኮሮና ቫይረስን መለየት የሚችለው የፈጠራ ውጤት ደግሞ ‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› በጤናው ዘርፍ ካበለፀጋቸው ቴክኖሎጂዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ ቴክኖሎጂ መረጃዎችን ከምስሎቹ ወስዶ በመተንተን አንድ ሰው በኮሮና ቫይረስ መያዙንና አለመያዙን ያሳውቃል። ከዚህ በተጨማሪም የወባ በሽታ አምጭ ትንኝ ዝርያን ለመለየት የሚያስችል ቴክኖሎጂም ሰርቷል።

‹‹ከ45 በላይ የወባ ትንኝ ዝርያዎች አሉ። ከእነዚህ መካከል በሽታውን የሚሸከሙት አምስቱ ብቻ ናቸው። ይህን ለመለየት ወደ መስክ በመውጣት ትንኞችን ከመያዝ ጀምሮ በትልልቅ ማሽኖች የተደገፈ የሥራ ሂደትን ማለፍ ይጠይቅ ነበር። የደቦ ቴክኖሎጂ ግን የትልልቅ ማሽኖችን እገዛ ሳይፈልግ በፎቶ ወይም በቪዲዮ ብቻ የትንኞቹን ዝርያ ለመለየት ያስችላል›› በማለት ጃርሚያ ያስረዳል።

ቡና ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ ከምታቀርባቸውና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ከምታገኝባቸው ምርቶች መካከል ቀዳሚው እንደሆነ ይታወቃል። ለአብነት ያህል በ2014 ዓ.ም ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ ካቀረበችው ቡና አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር አግኝታለች። ኢትዮጵያ በዘርፉ ካላት አቅም አንፃር ከዚህም በላይ ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባት ይገለፃል። ከዘርፉ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን በሚደረገው ጥረት ሊከናወኑ ከሚገባቸው ተግባሮች መካከል የቡና ምርት እንዲቀንስ የሚያደርጉ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር አንዱ ነው።

‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› ለዚህ አይነቱ ችግር መፍትሄ የሚሆን የቴክኖሎጂ ውጤት በማስተዋወቅ የቡናን ምርታማነት ለመጨመር ጥረት እያደረገ ነው። ቴክኖሎጂው በሽታው ስር ሰዶ የቡናውን ምርታማነት ከመጉዳቱ በፊት ለመለየትና ለመቆጣጠር ጥቆማ የሚሰጥ ከመሆኑ በተጨማሪ በሽታውን ለማስቆም የሚያስችሉ ምክሮችንም ይጠቁማል። ይህ ቴክኖሎጂ ከፎቶና ቪዲዮ በሚወሰዱ መረጃዎች በሽታዎቹን የሚጠቁም ሲሆን፤ ሰፋፊ እርሻዎችን በቀላሉ ለመከታተልና ለመቆጣጠርም ያስችላል።

በሌላ በኩል ፈጣንና ውጤታማ በሆነ መልኩ ቡናን እንደየደረጃው በመለየትና በመመደብ ለገበያ የማቅረብ ጉዳይም ለአብዛኛው አርሶ አደር ቀላል የሚባል ስራ አይደለም። ‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› የቴክኖሎጂ ተቋምም ይህን ችግር ታሳቢ ያደረጉ የፈጠራ ውጤቶችን ይፋ አድርጓል። ከእነዚህ መካከል አንዱ የቡና ደረጃዎችን የሚመድብ ቴክኖሎጂ ነው። ‹‹ቡና ቀዩ /የደረሰ/ና በጣም የደረሰ ፣ ያልደረሰ የሚባሉ ደረጃዎች አሉት። ወደ መፈልፈያ ማሽን የሚሄደው ቀዩ ቡና ብቻ ነው። የቡና ደረጃዎችን በመመደብ በየዓይነታቸው የሚለየው ቴክኖሎጂ ግን ቡናውን ወደ ኮንቴይር በማስገባት የደረሰውን ወደ ማጠቢያ ማሽኑ ይወስዳል፤ ሌሎቹን ደግሞ የደረቁ/የበሰሉ መሆንና አለመሆናቸውን ለይቶ ወደ ሌላ ቦታ ይወስዳቸዋል›› ሲል ያብራራል።

አብዛኞቹ የቡና ገበሬዎች ማሽን እንደሌላቸው የሚናገረው ጃርሚያ፤ ‹‹ገበሬዎቹ ማሽን ስለሌላቸው ቀዩን ቡና በዝቅተኛ ዋጋ ስለሚሸጡት ተጠቃሚ አይሆኑም። ስለሆነም ደቦ ኢንጂነሪንግ ይህን የገበሬዎቹን ችግር ለማቃለል በአነስተኛ ዋጋ የምትገዛ፣ ገበሬዎቹ በቀላሉ መጠቀም የሚችሏትና በፀሐይ ኃይል የምትሰራ ቀላል ማሽን እየሰራ ይገኛል›› በማለት ተቋሙ ለአርሶ አደሮች ችግር መፍትሄ እየፈለገ እንደሆነ ይገልፃል።

ከዚህ በተጨማሪም አትክልቶችን እንደጥራት ደረጃቸው የሚመድብ ማሽንም አስፈላጊ በመሆኑ፣ ‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› አቮካዶ እና ቲማቲም ምርቶችን ጥራት እየለካ የሚመድብና ለቀጣይ አገልግሎት ዝግጁ የሚያደርግ ማሽን ናሙናውን ሰርቶ አጠናቋል።

### የአፈር መመርመሪያ መሳሪያ

‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› ያስተዋወቀው ሌላው የፈጠራ ስራ የአፈር መመርመሪያ መሳሪያ ነው። ተቋሙ ከጅማ ዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ ተማሪዎች ለሚያመጧቸው የፈጠራ ፕሮጀክቶች ምክረ ሃሳቦችን በመስጠት በአጋርነት ይሰራል። ‹‹አሚሽቱ ጆይ›› ከተባለው ተቋም ጋር በትብብር የሰሩት የአፈር መመርመሪያ መሳሪያም የዚሁ አካል ነው። ይህ ቴክኖሎጂ ከመሬት የአፈር ናሙና በመውሰድ አፈሩ ምን ዓይነት ንጥረ ነገሮችን እንደያዘ፣ ለየትኞቹ ሰብሎችና ተክሎች ተስማሚ እንደሆነና ተጨማሪ ምክረ ሃሳቦችን የያዘ ሲሆን ምርታማነትን በመጨመር ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል።

እንደ ጃርሚያ ማብራሪያ፣ የአፈር መመርመሪያ መሳሪያዋ በቀላሉ መንቀሳቀስ የምትችልና በመጠንም ትንሽ ናት። ናሙናውን መለየት የሚያስችሉ ሴንሰሮች (Sensors) አሏት። መሳሪያዋን አፈር ውስጥ በማስገባት የአፈሩን ናሙና በመውሰድ የአፈሩ መረጃ (የአፈሩ ንጥረ ነገር ይዘት፣ የሙቀት መጠን፣ እርጥባማነት ...) ወደ ሞባይል መተግበሪያ (Applications) እንዲተላለፍ ይደረጋል። የአፈሩ ዝርዝር መረጃም ይታወቅና ለየትኛው ሰብልና እፅዋት ተስማሚ እንደሆነ ይታወቃል።

በ2013 ዓ.ም የተሰራው ይህ የአፈር መመርመሪያ ቴክኖሎጂ ዓለም አቀፍ ሽልማትን ያሸነፈ ሲሆን ተጨማሪ ማሻሻያዎች ተደርገውበት በቅርቡ ለገበያ የሚቀርብ ሆኖ እንደሚወጣ ይጠበቃል። መሳሪያው በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ፣ በሶማሊኛ፣ በካፊቾ፣ በወላይትኛ እንዲሁም በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች አገልግሎት እንዲሰጥ ሆኖ የተሰራ ሲሆን በሌሎች ተጨማሪ ቋንቋዎችም አገልግሎት እንዲሰጥም ተደርጎ እየተሰራ ነው።

የአፈር ምርመራ የሚከናወንባቸው ማዕከላት ውድ የሆኑና በቀላሉ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የማይችሉ ግዙፍ መሳሪዎች የሚገኙባቸው በመሆናቸው ምርመራውን እጅግ ፈጣን በሆነ ጊዜና በየትኛውም ቦታ ለማከናወን አዳጋች ይሆናል። የ‹‹ደቦ ኢንጂነሪንግ›› እና የ‹‹አሚሽቱ ጆይ›› የትብብር ውጤት የሆነው የአፈር መመርመሪያ መሳሪያ በመጠን አነስተኛ እንዲሁም በቀላሉ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችል መሆኑ የአፈር ምርመራ ስራውን ቀላልና ቀልጣፋ ያደርገዋል። የአፈር መመርመሪያ መሳሪያው በአንድ አካባቢ ዘር ከመዘራቱ በፊት አፈሩ ለየትኛው የዘር ዓይነት ምቹ እንደሆነ በመለየት የምርት ውጤትን ከፍ ለማድረግ ያግዛል።

የአፈር መመርመሪያ መሳሪያውን ለመስራት የሚያገለግሉ ሴንሰሮችን በቀላሉ ማግኘት አለመቻል የስራው ዋነኛ ፈተና መሆኑን ጃርሚያ ይናገራል። ‹‹ሴንሰሮቹን እንደልብ ማግኘት አይቻልም። ሴንሰሮቹ በውድ ዋጋ የሚገዙ በመሆናቸው መሳሪያው ተሰርቶ ለገበያ ሲቀርብ ዋጋው ውድ ይሆናል። ግብዓቶቹን በቀላሉ ማግኘት ከተቻለ መሳሪያውን በብዛት ለማምረትና ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ለማቅረብ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል›› ይላል። ከዚህ በተጨማሪም የፈጠራው ባለቤቶች ውድድሮችን እያካሄዱ ከሚያገኙት ገንዘብ በስተቀር ድጋፍ የሚያደርግላቸው ሁነኛ አካል እንደሌለም ጃርሚያ ይገልፃል።

እንዲህ አይነት የቴክኖሎጂ ውጤቶች መንግስት ዲጂታል ኢትዮጵያን ለመገንባት ለያዛቸው ስራዎች ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፤ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር መሰል ስራዎችን የሚደግፉበት አግባብ ስለመኖሩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከዚህ አኳያም በቅርቡ በስራና ክህሎት ሚኒስቴር የእውቅናና ሽልማት መርሀ ግብር ተካሂዷል። ሚኒስቴሩ አዳዲስ የፈጠራ ስራዎች ለስራ እድል ፈጠራ ወሳኝ መሆናቸውን ያምናል።

ደቦ ኢንጂነሪግም ሆነ በሌሎች ቴክኖሎጂ ፈጠራ ላይ የሚሰሩ አካላትም ከሚኒስቴሩና ሌሎች አጋር አካላት ጋር ለመስራት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፤ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ሆነ ሌሎች ቴክኖሎጂዎች ላይ የሚሰሩ መንግስታዊም ሆኑ ያልሆኑ ተቋማት በፈጠራ ስራ ላይ አተኩረው የሚሰሩ ግለሰቦችን፣ ድርጅቶችን ፈልገው በመደገፍ የፈጠራ ስራዎች ዜጎችንም አገርንም ተጠቃሚ ማድረግ፣ ዲጂታል ኢትዮጵያን የመገንባቱን ጥረትም ማጠናከር ይጠበቅባቸዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ለውጭ ምንዛሬ እድገት ተስፋ የተጣለበት የቡና ምርት

**ማህሌት አብዱል**

ቡና ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልካቸው የግብርና ምርቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀስ ከመሆኑም በላይ ለዘመናት የአገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሆኖ ቆይቷል። ሆኖም ከማሳ እስከ ገበያ ድረስ ባለው ኋላቀር አሰራር ምክንያት አገሪቱ በዚህ የተፈጥሮ ፀጋዋ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ ሳትሆን ቀርታለች። ይህንን ችግር ለመፍታትና በዘርፉ የላቀ ተጠቃሚ ለመሆን ውስን ጥረቶች ቢደረጉም ይሄነው የሚባል ውጤት ማምጣት ያለመቻሉ የብዙዎች የዘመናት ቁጭት እንደሆነ እሙን ነው።

ከሰሞኑ ግን ልብን የሚያሞቅ ዜና ተሰምቷል። ይኸውም አገሪቱ የቡናን ምርት ለዓለም ገበያ ማቅረብ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ፍፁም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ 300 ሺ ቶን ቡና በመላክ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቷ ነው። በብዛትም ሆነ በጥራት ረገድ የተሻለ ምርት ይዞ በመቅረብ የማይደፈረውን የዓለም የቡና ገበያ ሰብሮ ለመግባት እንደተቻለ ከቡና ሻይ ባለስልጣን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። ይህ ብቻ ሳይሆን አንድ አርሶ አደር «በካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ» ዓለም አቀፍ ውድድር አንድ ኪሎ ልዩ ጣዕም ያለው ቡና በማቅረብ 884ሺ ዶላር ብር ማስገኘት መቻሉ ትልቅ መነቃቃት ፈጥሯል።

ከዚህ በመነሳትም በተያዘው በጀት ዓመት ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማግኘትና 45 በመቶ ብላጫ ያለው አፈፃፀም ለማስመዝገብ በመንግስት ታቅዷል። ይህንን እቅድ በምን መልኩ ማሳካት ይችላል? ካለፉት ዓመታት የተሻገሩ የተንዛዙ አሰራሮችንና ችግሮች በምን መንገድ መቅረፍ ይገባቸዋል? ስንል የዘርፉን ባለሙያዎች አነጋግረናል።

የቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ እንደሚሉት፤ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በዘርፍ የተገኘው ገቢ በበጀት ዓመቱ ይገኛል ተብሎ በዕቅድ ከተያዘውም ሆነ ከቀዳሚው ዓመት ጭምሬ ያሳየ ነው። ይህ የውጭ ምንዛሪ ግኝት በቡና የወጪ ንግድ ታሪክ ከግማሽ ቢሊዮን ዶላር በላይ ብላጫ የተገኘበት ነው።

ይህ ውጤት ከመገኘቱ በፊት ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የቡና ወጪ ንግድ የተወሰኑ መሻሻሎች ቢታዩበትም፤ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማግኘት ታቅዶ ማሳካት ሳይቻል ቀርቷል። አሁን ግን ከቡና የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ መሻገር መቻሉ ትልቅ እምርታ ነው። በተያዘው በጀትም ዓመት ከ45 በመቶ በላይ ብልጫ ያለው ገቢ ለአገር ማሳገባት እንደሚቻል እምነት አሳድሯል።

የአሁኑ የቡና ወጪ ንግድ ገቢ ማደግ ዘንድሮ የታየው የዓለም ቡና ዋጋ በመጨመሩ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይነሳል። ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፤ ግን የዓለም የቡና ዋጋ መጨመር አገሪቱ ላስገኘችው የላቀ ገቢ እንደ አንድ ምክንያት ቢጠቀስም በጥቅል ሲታይ ግን የሪፎርም ሥራው ትልቅ ለውጥ በማምጣቱ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በበጀት ዓመቱ የዚህን ያህል የውጭ ምንዛሬ ቡና ሊያስገኝ ከቻለባቸው ምክንያቶች ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የቡና ዋጋ እያደገ መምጣትና የብራዚልና የኮሎምቢያ ቡና በውርጭ መመታት እንደሆነ የዘርፉ ተንታኞች ያስረዳሉ። ዶክተር አዱኛ በበኩላቸው፤ ከቡና ምርት ጋር በተያያዘ በተሰራው ሪፎርም ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት የቡና ምርት እያደገ መምጣቱም አንድ ምክንያት እንደሆነ ነው ያስረዱት።

የሪፎርም ስራውም የተሻለ ገቢ እንዲገኝ ወሳኝ ሚና መጫወቱን ጠቅሰው፤ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ ግብይት ይፈፀም እንደነበረና ካለፈው ዓመት ጀምሮ ግን የተለያዩ የገበያ አማራጮችን በመፍጠር ገቢውን የዚያኑ ያህል



ዶ/ር አዱኛ ደበላ

ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

ማሳደግ መቻሉን ያብራራሉ። በዚህ ሪፎርም መሠረት አርሶ አደሩ በተወሰነ መልኩ ተጠቃሚ እያደረጉት ስለሆነ ምርቱ ቶሎ ቶሎ እያወጣ እንዲሸጥ አስችሏል ይላሉ።

ቀደም ሲል በኮንትሮባንድ የሚወጣው ቡና አሁን ላይ አርሶ አደሩም ሆነ ሌላውም ተዋንያን የተሻለ ገቢ ስላገኙበት ወደዚህ ሥርዓት እየገባ በመምጣቱ ውጤቱ ተገኝቷል። በጥቅሉ በአገር ውስጥ የተሠራው ሪፎርምም ሆነ የዓለም የቡና ዋጋ መጨመርና እንደ ብራዚል ያሉ ዋነኛ ቡና ላኪ አገሮች ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በገበያቸው ላይ የገጠማቸው ክፍተት ለኢትዮጵያ መልካም ዕድል የፈጠረ ሆኗል።

የንግድና ኢንቨስትመንት አማካሪ አቶ አማንይሁን ረዳም፤ ባለፈው በጀት ዓመት የተገኘው ገቢ እንደትልቅ ስኬት የሚታይ መሆኑን ያምናሉ። በተለይ ባለፉት ዓመታት ከነበረው አፈፃፀም አንፃር ሲታይ ጥሩና የሚበረታታ እንደሆነ ያስረዳሉ። ይህ ውጤት የብዙ ነገር ድምር ውጤት እንደሆነ አመልክተው፤ አንደኛው ምክንያት የሚላከው የቡና መጠን መጨመሩ እንደሆነ ያነሳሉ። ይህም ደግሞ የአርሶ አደሮች የልፋት ውጤት መሆኑ የማይካድ ሃቅ እንደሆነ ነው የተናገሩት። ዘርፉን የሚመሩት የመንግስት፤ የግል ባለሃብቶች እንዲሁም የልማት አጋሮች ርብርብ ማድረጋቸውም ሌላው አብይ ምክንያት እንደሆነም ይጠቅሳሉ።

«ዘንድሮ ደግሞ መንግስት ያቀደው ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለማምጣት ነው። ይሄ ማለት የባለፈውን ዓመት አፈፃፀም ወደ 45በመቶ ያህል ማሳደግ ማለት ነው። በእኔ እምነት ይሄ ይቻላል። ባለፈው ዓመት ምርት መጠኑ የጨመረበት ገቢ ያደገበትም ሁኔታ ሲታይ ዘንድሮ የታሰበው ገቢ የሚሳካ ነው» ይላል።

ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ለቡና ከፍተኛ የሚመች አየር ንብረት፤ ሰፊ መሬት ያላት መሆኑ እንዲሁም ከማሳ ጀምሮ እስከ ግብይት ያለውን አሰራር ማዘመን ከተቻለ የማይሳካበት ሁኔታ እንደሌለ ይገልፃሉ።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በርካታ ወጣቶችን ወደ ግብርናው እንዲገቡ በማድረግ ዘመናዊ እርሻ ዘዴን ማስተማር ያስፈልጋል። ወጣቶቹን በደንብ እያስተማሩና እያሰለጠኑ ከምርምር ጣቢያዎች ጋር ተቀናጅቶ መስራት ይገባል። የተሻለ ዝርያ ወደ አርሶ አደሩ ማሳ የሚገባበት ሁኔታ፣ የብድርና የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ የቴክኒክ ድጋፍ በደንብ ከተመቻቸና የቡና ተክል የሚስፋፋ ከሆነ፤ በሚቀጥሉት ዓመታት የተሻለ ምርታማ የማይኮንበት ምክንያት አይኖርም። ምርታማነቱ ባደገ ቁጥርም ከቡና ዘርፍ የሚገኘውም ገቢ በዚያው ልክ እያደገ ይመጣል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ባለ ልዩ ጣዕም (ስፔሻሊቲ ቡና) በስፋት ማምረት እንደሚገባ አቶ አማንይሁን ይናገራሉ። «ባለልዩ ጣዕም ቡናውም ሆነ መደበኛ ጣዕም ያለው በአንድ ማሳ ውስጥ የሚበቅሉ ናቸው።



አቶ አማንይሁን ረዳ

ልዩነቱ አያያዝ ነው» ይላሉ። ባለልዩ ጣዕም ዘርፍ ያለ ቡና አስተራረሙም ሆነ በፀሐይና በዝናብ ጊዜ አያያዙ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት እንደሆነ ያነሳሉ። ፍሬው ከተለቀመ በኋላ ያለውን አሰራር ሲያስረዱም «ፍሬው የሚደርቅበት፣ የሚታጠብበትና አጠቃላይ ሂደቱ እጅግ ጥንቃቄ የሚፈልግ ነው» በማለት ይናገራሉ።

በተቃራኒው ደግሞ ኮሜርሻል ግሬድ የሚባለውና በመደበኛ መንገድ የሚከናወን የምርት ሂደት ግን በተለየ መልኩ ብዙ የማያደክም ቢሆንም ከገቢ አንፃር ለአገር ያለው ጠቀሜታ አነስተኛ መሆኑን ነው የሚያብራሩት። «ከገቢ አንፃር ግን ስንመለከተው ባለልዩ ጣዕም ቡና የሚባለው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል። ስለዚህ አርሶ አደሮቻችን ባላቸው ማሳ የቡና አያያዛቸውን ዘዴ እንዲያዘምኑ ብናስተምራቸው፤ ዘመናዊ የግብርና እውቀት እንዲኖራቸው በደንብ ቢሠራና ክትትል ቢደረግላቸው ገቢያቸውም በዚያው ልክ ሶስትና አራት እጥፍ ሊያድግ የሚችልበት ሰፊ እድል አለ» ሲሉ ያብራራሉ።

እንደ አቶ አማንይሁን ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከው ቡና በዋናነት ከመደበኛ ጣዕም ያለው ወደ ልዩ ጣዕም ያለው ቡና የሚሄድበት ሁኔታ ከተመቻቸ የቡና ምርት መጠን እንኳን ባይጨምር የቡና ጥራቱ ከተሻሻለ ገቢያችን ይጨምራል። ለዚህ ደግሞ ምርቱ ምሳ ላይ እያለ በደንብ መንከባከብ ይገባል። አንዱን ከሌላው ምርት ሳይቀላቀል ተለቅሞ ታጥቦና ተዘጋጅቶ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ታሽጎ ቡናው ጣዕሙን እንደጠበቀ ተደርጎ መላክ አለበት። እያንዳንዱን ሂደት ደግሞ በአግባቡ የሚከታተል አካል ሊኖር ይገባል።

«በተመሳሳይ ከዚህ ቀደም እሴት ጨምረን ቆልተን ፈጭተን ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አሽገን ፕሪምየም ዋጋ ለሚገኝባቸው የአውሮፓ፣ የአሜሪካ የቻይና የጃፓን ገበያ የምናቀርብ ከሆነ በአንድ በኩል ለአገራችን ኢንደስትራላይዜሽን መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል። በሌላ በኩልም ለወጣቶቻችንም የስራ እድል ይፈጥራል» ሲሉ ቡናው ደግሞ እሴት ተጨምሮበት በሚላክበት ሰዓት የተሻለ ዋጋ የሚያስገኝ መሆኑን ነው ያስገነዘቡት።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ የዛሬ 35 ዓመት አንድ የቡና ተክል የሌላቸው አገሮች ዘሩን ከኢትዮጵያ፤ ከኮሎቢያና ከብራዚል ወስደው ዛሬ ከዓለም ሁለተኛ ቡና ላኪ የሆኑ አገሮች አሉ። ከእነዚህም መካከል ቬትናም በዋናነት የምትጠቀስ ሲሆን አገሪቱ በዓመት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ታገኛለች፤ አሁን ከብራዚል ቀጥሎ ትልቋ የዓለም ቡና ላኪ አገር መሆን ችላለች። በአንፃሩ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ አንደኛ፤ ከዓለም ወደ አምስተኛ ደረጃ ላኪ አገር እንደመሆንዋ ጥራት ላይ ትኩረት አድርጋ ስትሰራ በቅርቡ ከዓለም ሶስተኛ የምትሆንበት ሰፊ እድል አላት።

ይህ እንዲሆን በተለይ መንግስት ለቡና ልማት ሰፊ ትኩረት ሰጥቶ ኢትዮጵያ የቡና መገኛ አገር ብቻ ሳትሆን አቅራቢ እንድትሆን የበለጠ መትጋት አለበት ይላሉ። በተጨማሪም የአገሪቱን ገፅታ ለማሻሻል ቡና ከነአፈላሉ ስርዓቱ የቱሪስት መስህብ የሚሆንበትን ሁኔታ በማመቻቸት በቡና ላይ የሚደረጉ ወርክሾፖች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ማድረግ ይገባልም ባይናቸው።

«ኢትዮጵያ በዘርፉ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን አሁንም ምርት የተሻለ ጣዕም ያለው ቡና ማዕከልነቷን ለዓለም በማሳየት፤ ቡና ልኮ ከሚገኘው ገቢ ባልተናነሰ በቡና ምክንያት ከቱሪዝም የሚገኘውን ገቢ ታሳቢ ማድረግና ማሳደግ ይቻላል» በማለት ይናገራሉ። እቅዱ ግቡን እንዲመታ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብና የተቀናጀ የጋራ ጥረት ይፈልጋል።

እንደአቶ አማን ማብራሪያ፤ ከሁሉ በላይ ዘመናዊ የገበያ ስርዓትን መገንባት ላይ ትልቅ ትኩረት አድርጎ መስራት ያስፈልጋል። በተወሰኑ የኮንትራት እርሻዎች የምርት ብክነትንም፤ የኮንትሮባድ ንግድንም ለማስወገድ እየተሰራ ያለውን ማስፋት ይገባል። በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በኩል ደግሞ አርሶ አደሮች በዩኒየናቸው፣ በህብረት ስራ ማህበራታቸው አማካኝነት ምርታቸውን ጥራቱን እያስጠበቁ፤ እያስፈተሹ ጥራቱን እያረጋገጡ አርሶ አደሩ በቀጥታ ገዢዎች በግልፅ ጨረታ የሚሳተፉበት የግብይት ስርዓት መጠናከር አለበት።

የብሔራዊ ባንክ በቅርቡ የወጣ መመሪያ አጋዥ እንደሆነም ይነሳል። ከወቅታዊው የዓለም የቡና ዋጋ መጨመር ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ በዚህ አጋጣሚ የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን በቅርብ ከተወሰዱ ዕርምጃዎች መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባልተለመደ መልኩ ለቡና አቅራቢዎችና ላኪዎች ባንኮች ብድር እንዲሰጡ ውሳኔ ላይ መድረሱ ነው። ብሔራዊ ባንክ የወሰነው ይህ ውሳኔ ባንኮች በብሔራዊ ባንክ ከሚገኘው የመጠባበቂያ ገንዘባቸው ላይ ሁለት በመቶውን በመውሰድ ለቡና አቅራቢዎችና ላኪዎች ብድር ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን ነው። ይህም ዕድሉን ለመጠቀም መልካም አጋጣሚ እንደፈጠረ ይታመናል ይላሉ።

በዚህ ረገድ ቀደም ሲልም አርሶ አደሮች በተለይ በብድርና ቁጣባ፤ በስራ ማህበራት በኩል ማዳበሪያና ምርጥ ዘር በብድር ያገኙ እንደነበር አቶ አማን ይናሳሉ። ይሁንና ብድሩ ከፍተኛ ወለድ የሚከፈልበት መሆኑ ትርፋማነታቸው ላይ የራሱን ጫና አሳድሮ እንደነበር ያስታውሳሉ። « በነፃ ይሰጣቸው ባይባልም እንኳን የአስተዳደር ወጪን መሸፈን በሚያስችል መንገድ ዝቅተኛ ሆኖ መቅረብ አለበት» ይላሉ። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በቀጥታ ለአርሶ አደሩ ባሉት ቅርንጫፎች የቁም እንስሳትን መያዢያ በማድረግ አበድራለሁ ማለቱ በጣም ጥሩ ውሳኔ እንደሆነ ይናገራሉ።

በበጀት ዓመቱ የቡና ዘርፍ ለውጭ ምንዛሬ ግኝት የተጣለበትን ሚና ይወጣ ዘንድ ከምንም በላይ ዘመናዊ አሰራር መዘርጋትና ወደ ተግባር መግባት ይጠበቃል። በተለይ ኢትዮጵያ የአርሶ አደር አገር እንደመሆንዋ፤ ኢኮኖሚውን በሻካራ መዳፉ ደግፎ የያዘ፤ ገጠሩን ከተማውን እየመገበ የሚገኝ የሕብረተሰብ ክፍል እንደመሆኑ ትልቅ ትኩረት መስጠት ሊሰመርበት ይገባል። ምክንያቱም ለአርሶ አደሩ የማትመች ኢትዮጵያ ዘላቂ የሆነ ልማትም ሆነ ሰላም አይኖራትም። ለአርሶ አደር የሚመች አገር መፍጠር ይገባል። ምርታማቱን እንዲያሳድግ ማስተማር ለነገ የሚታው አይደለም። ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ልናስተዋውቀውና አማራጭ የብድር መንገዶች ሊሰፉለት እንዲሁም በዝቅተኛ ወለድ ግብዓት እንደልብ የሚገዛበት፤ የገንዘብ አቅርቦትና የገበያ እድሎችና ትስስሮች መፍጠር ዘርፉን ለማሳደግ ወሳኝ መሆናቸውን በመፍትሄነት አመላክተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የፊልምና ቲያትር ንግስቷ

**ሰላማዊት ውቤ**

‹‹ያኔ እኔ ራስ ቲያትር እሰራ በነበረበት ጊዜ የወሊድ ፈቃድ 40 ቀን ነበር። የአመት ፍቃዴን ተጠቅሜ የ40 ቀን ፍቃዴን ወሰድኩ፡፡ እንዲህም ሆኖ የመጀመሪያ ልጄን ወልጄ እተኛሁበት አራስ ቤት ቲያትር እንዳዘጋጅ ስክሪፕት ተላከልኝ›› ትላለች የዛሬዋ እንግዳችን፡፡

እንኳን ባል ቀርቶ ወጣ ወጣ ያለ እንደ ቲያትር ያለ ሙያን ወላጅ እንኳን በማይፈልግበት ማህበረሰብ ውስጥ አልፎና ራስን ሆኖ ለስኬት መብቃት እጅግ እንደሚከብድም ታወሳለች። ትዳር፣ ልጅ፣ ፊልምና የቲያትር ሥራ ውጪ በማምሸት፣ውጭ በማደር፣ ከአዲስ አበባ ውጭ በመውጣት የሚሰራ መሆኑ ክብደቱን ከመጠን በላይ እንደሚገዝፈውም ከራሷ ተሞክሮ ተነስታ ትመሰክራለች።

እንደ ዕድል ሆኖ እሷን ባይገጥማትም ቀናተኛ ባል ካለ ደግሞ የበለጠ ክብደቱ ይጎላል። ከባድ ቢሆንም ይሄን ጊዜ ጉልበት የሚሰጠው እግዚአብሔር እንዲሁም በቅርቡ በሞት የተለያት ባለቤቷና የሁለት ወንድ ልጆቿ አባት መልካምነት አግዟት በቲያትሩና በፊልሙ ዓለም ከ35 ዓመታት በላይ መናኘት ችላለች።

‹‹ማንም ሰው ቢያግዝ እናት እናትነቷን አትተውም›› ስትል ምንም በቲያትርና ፊልም ሥራ ጫና ውስጥ ብትኖርም በተለይ ለልጆቿ የሚያስፈልጋቸውን ሳታሰልስ ታደርግላቸው እንደነበር ትናገራለች። አሁንም ከጥበቡ ሳትወጣ በታምራት ፊልም ፕሮዳክሽን እየተሰራ ባለ ፊልም ላይ በፕሮዳክሽኑም፣ በፊልሙም የአክቲንግ ዳይሬክተር ሆና እየሰራች ትገኛለች።

ዛሬ እንግዳችን ያደረግናት አርቲስት ዓለምፀሐይ በቀለ ወሊድን ብቻ ሳይሆን ከሴትነት ጋር ተያይዞ በኪነጥበቡ ሙያ ዘርፍ ሊገጥሙ የሚችሉ ከባድ መሰናክሎችን ተሻግራለች። በአጫጭርና የሙሉ ጊዜ ቲያትሮች፣ የቴሌቪዥን ድራማዎች በዝግጅት፣ በትወና እና በመፃፍ ተሳትፋለች።

‹‹ወንድ አይገባም›› የሚለውንና ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤት ለመድረክ የበቃውን ጨምሮ ራሷ ጽፋና አዘጋጅታ ለመድረክ ባበቃቻቸው ስድስት ያህል ተወዳጅ ቲያትሮቿ ተለይታ የምትታወቀው አርቲስቷ አብዛኞቹን ቲያትሮች፣ ፊልሞችና የቴሌቪዥን ድራማዎች በመሪ ተዋናይነት ነው የተጫወተቻቸው። ለሴት ልጅ በቲያትር መሳተፍ ከባድ ነው። ገና ልጃቸው በሙያው እንድትሰማራ ባለመፍቀድ ከወላጆች ይጀምራል። ሥራ ላይም ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ሆን ተብሎ ሳይሆን ግንዛቤ ካለመኖር ሊከሰት ይችላል። እሷ ይሄን ሁሉ ችላ በመሻገሯ በቅርቡ 10ኛውን የ2014 የበጎ ሰዎች ሽልማትን አግኝታለች። በሽልማቱ ዓለምፀሐይን ጨምሮ ከዘጠኝ የተለያዩ ዘርፎች 691 ለአገር በጎ ያደረጉ እጩዎች ቀርበው ነበር። በየዘርፉም ሦስት፣ ሦስት ተለይተው ቀሩ። በኪነጥበቡ ዘርፍ ከተለዩት ሦስት ለአገርና ለሕዝብ አርአያነት ያላቸው አሸናፊዎች መካከልም ዓለምፀሐይ በፊልም ዳይሬክተሪንግ ተሸላሚ መሆን ችላለች።

‹‹እቴጌ መነን የሴቶች ትምህርት ቤት እማር በነበረበት ጊዜ ወንድ ስለሌለ ሴቶች ነበርን እንደ ወንድ ሆነን በትምህርት ቤቱ በሚዘጋጁ ድራማዎች የምንተውነው›› የምትለው ዓለምፀሐይ አሁን ታዋቂ ወዳደረጋት የቲያትርና የፊልም ሙያ ለመግባት መነሻ የሆናትን ታስታውሳለች።ሁለት ወራት የቆየችበት የጋሽ ተስፋዬ አበበ የቲያትር ክበብም አስተዋጽኦ እንዳደረገላት ታነሳለች። ክበብ ውስጥ ሳለች የእጩ ተዋናይ ኮርስ በመምጣቱ ከክበቡ ወጥታ ለሁለት ዓመታት ኮርሱን ወስዳለች። ወደዚያው ራስ ቲያትር ተከፈተ። እሷን ጨምሮ ኮርሱን የወሰዱት ተማሪዎች በሙሉ አዲስ ሠራተኞች ሆነው በራስ ቲያትር ተቀጠሩ። አርቲስቷ እዚህ ቲያትር ቤት እዛም እዚህም እንድትሳተፍ የሚጋብዟት ሲበዛ በራሷ ፈቃድ መልቀቂያ አቅርባ እስከለቀቀች ድረስ ለ25 ዓመታት አገልግላለች። ከ30 በላይ የመድረክ ቲያትሮችን በተዋናይነት ተጫውታለች። ከራስ ቲያትር ከወጣች በኋላ ስድስት ያህል የሙሉ ጊዜ ቲያትሮች አዘጋጅታለች። ከዚህ በኋላም የቴሌቪዝን ድራማና ፊልም በስፋት አዘጋጅታለች። እንዲሁም እነዚህ ፊልሞችና ቲያትሮች ላይ በትወና ሰርታለች። ገመና የቴሌቪዢን ድራማ ላይ ከሦስቱ መምህራን አንዷ የነበረችበት ይጠቀሳል።

እንደምትለው ፊልምና ቲያትር ከትዳር፣ ልጅ፣ የቤት ኃላፊነቶች ጋር ውጭ በማምሸት፣ ውጭ በማደር፣ ከአዲስ አበባ ውጭ በመውጣት የሚሰራ በመሆኑ



**አርቲስት ዓለምፀሐይ በቀለ**

ይከብዳል። እንደዚህ ዓይነት ሥራዎች በጣም አቅምና ጊዜ ይጠይቃሉ። አንዳንድ ጊዜ ቤታችንን በሀሳብ ጭምር ላናየው እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ ቤትም ውጭም እንሰራለን። በአርቲስቶች ላይ ሲሆን ይታይና ይጎላል እንጂ ሴቶች በአጠቃላይ የሥራ ሰው ሲሆኑ ይሄ ችግር ይገጥማቸዋል። ብዙዎች ለስኬት የበቁት ይሄን ሁሉ መሰናክል ተወጥተው ነው። በዚህ ሙያ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሙያ ቢሆን ሴት ምንም ነገር መሥራት ትችላለች። ይሄን ማንም ሰው ማመን አለበት። በመጀመሪያ መጠንከር፣ በቀጣይ እንደሚችሉ እርግጠኛ መሆን ይኖርባቸዋል። የሴት ጭንቅላት ብዙ ነገር ማሰብ ይችላል። ትዳሯን፣ ልጆቿን፣ ሥራዋን፣ ሁሉን ነገር ማሰብ ትችላለች። ‹‹ሴቶች አእምሯችን ውስጥ የምንሰራው ሥራ ነጠላ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በጣም የሚያጨናንቀን ሥራ ሊኖር ይችላል። ግን በድል መወጣት ይጠበቅብናል›› ትላለች። እንደ እሷ የቲያትር ፊልም ደራሲዎች ብዙ ጊዜ የወንድ ካራክተሮችን (ገፀ ባህሪዎችን) ነው አብዝተው የሚጽፉት። ለሴቶቹ አነስተኛ ነገር ነው የሚጽፉት። ብዙ ሴት ተዋናዮች ያልነበሩትም ለዚህ ነው። አሁን ግን እራሳቸው በሚያደርጉት ጥረት በዝተዋል። ‹‹ለምሳሌ እኔ አዘጋጅ የሆንኩት ከአንዲት ጓደኛዬ ጋር እስካሁን ድረስ ለወንዶቹ ረዳት አዘጋጅ ሆነን ብዙ ቲያትር ሰርተናል። አሁን ግን ራሳችንን ችለን ማዘጋጀት አለብን ብለን ጠይቀን ›› ነው ስትልም የራሷን ተሞክሮ አብነት ታደርጋለች። እንዳከለችው በአጋጣሚ በዚያን ጊዜ የነበረው ቲያትር ለሌላ ወንድ ተሰጥቶ ስለነበር የሚቀጥለውን ቲያትር ታዘጋጃለሽ ተብሎ የሚቀጥለው ቲያትር ተሰጣት። ከዛ ቀጥሎ የነበረውን ፤ ቲያትር ደግሞ ፕሮፖዛል አቅርባችሁ ያለፈ ሰው ያዘጋጃል ተባለ። አቀረበችና አለፈች አዘጋጀች። ቆየት ብሎም የቲያትር ክፍል አዘጋጅ ይመረጥ ሲባል የቲያትር ክፍሉ አባላት በድምፅ ብልጫ እሷን መረጧት። እንዲሁም የቡድን ዝግጅት ውስጥ ካለ ኮሚቴ እሷን የዝግጅት መሪ አድርገው መረጧት። እንዲህ እንዲህ እያለች ነው ራሷን ያበቃችው።

‹‹አሪፉ የነበረው ሁላችንም ተማሪዎች ስለነበርን ስሜታችን የሥራ ሳይሆን የትምህርት ቤት ዓይነት ነበር›› ስትል ዓለም ፀሐይ ያበቃትን የሥራ አሀዱዋን ታስታውሳለች። እንዳከለችልን ትምህርቷን አቋርጣ በገባችበት ራስ ቲያትር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰራችው ‹አንድ ለአንድ›የሚል ቲያትር ነበር።

ይሄ በወላጆቿ መሰማቱ በሙያው ከገጠማት መሰናክል ቀዳሚ ሆነ። በጥብቅ ተቃወሟት። ዓለምፀሐይ በማህል አጎቷ ደርሶላት በብዙ ትግል አሳምኗቸው ባይፈቅዱላት በሙያው ገፍታ ዛሬ ላይ መድረስ ትችል እንዳልነበርም ታወሳለች። እንደ እሷ አሁን ላለችበት የባለቤቷና የቤተሰቦቿ አስተዋጽኦ ጉልህ ነው። ቤተሰቦቿ ትምህርቷን በማቋረጧና የማይፈልጉት ሙያ ውስጥ በመግባቷ የተቃወሟት ቢሆንም የአቅማቸውን ደግፈዋታል።

ቤተሰብ ቢደግፈንም ብዙ ጊዜ ወልደን በምንተኛበት ጊዜ ነው ለምሳሌ፡-እኔ ስወልድ እናቴ ቤት እየሄድኩ ነበር የምታረሰው። ከዛም አልፎ ብዙ ጊዜ ታናናሽ እህቶቼ ሲመቻቸው መጥተው ያግዛሉ። ልጅ ያቅፋሉ። ወደ ቤት ይዘው ይሄዳሉ። ልጆቼን ከሰራተኛ ጋር ቤተሰቦቼ ቤት ወስጄ እንዲጠብቁልኝ በማድረግ ነበር ወደ ሥራ የምሄደው። ማታ ደግሞ ወደ ቤተሰቦቼ ጋር በመሄድ ልጆቼን ሰብስቤ ወደ ቤቴ እገባለሁ ስትል ድካሟን ትገልፀዋለች።

በተለይ የመጀመሪያ ልጇን ወልዳና የ40 ቀን የወሊድ ፈቃድ ብቻ ተሰጥቷት አራስ ቤት በነበረችበትና ይባስ ብሎ ቲያትር እንድታዘጋጅ አራስ ቤት ድረስ ስክሪብት በተላከላት ወቅት ትልቅ እገዛ አድርገውላታል። እገዛቸው በወሊድ ፈቃዷ ላይ የዓመት ፈቃዷን በመውሰድ ወጣ ገባ እያለች የተሰጣትን የቲያትር ዝግጅት የቤት ሥራ በስኬት እንድታከናውን ረድቷታል።

ሟቹ ባለቤቷ የሚያደርግላት እገዛም ቀላል አልነበረም። ሥራ በሌለው ጊዜ ልጆቹን ያጥባል። ልብሳቸውን ያዘጋጅና ያለብሳል። የቤት ሥራቸውን አስርቶ ይጠብቃታል። ያስተኛቻቸዋል። እሷ በእሱ ቦታ፣ እሱ በእሷ ቦታ ቢሆኑ ኖሮ አደርገዋለሁ ብላ የማትገምተውን መልካም ነገር ሁሉ አድርጎላታል።

አርቲስቷ ይሄን ከአንዳንድ በሙያው ውስጥ ያሉ ሴቶች በተለየ ከባለቤቷ ጋር ያላትን ትስስብ ከሌሎች ባሎች ጋር አታነፃፅረውም። ባለቤቴን እኔም አምነዋለሁ። እሱም ያምነኛል። አልዋሸውም ዕውነት ነው የምናገረው። ቅዳሜና እሁድ ሥራ እንዳለኝ ያውቀዋል። ፊልም ሲጀመር ፊልም እንደምሰራ ይረዳኛል። ሳመሽ እንዴውም ደውሎ ራት ይቀመጥልሽ ወይ ነበር የሚለኝ። አለዚያ እስከ ስንት ሰዓት እንጠብቅሽ ይለኝና የሚቻለውን ያህል ይጠብቃኛል ትላለች። አደውልና እናንተ ተኙ እኔ በጣም አመሻለሁ እላለሁ። መኪና ያደርስሻል ወይ ነው ጥያቄው። አዎ ያደርሰኛል እላለሁ›› ስትል ነግራናለች። የተከራዩባቸው የውጭ በር ቁልፍ ስለሰጧቸው በመጣችበት ሰዓት ከፍታ ትገባለች። በመሆኑም በባለቤቷ ላይ የቅናት መንፈስ አይታ አታውቅም። ‹እኔ እንዳልጎዳ ነበር የሚጠብቀኝ› ትላለች። ሌላው ቀርቶ ለምሰራው ሥራ ሁሌ ጉልበት የነበረኝ ባለቤቴ ነውም ባይ ነች። ዕድሉ ስለነበረው ለፊልምም ሆነ ለቲያትር ማንበብ የምትፈልገውን በአጠቃላይ ለምትሰራው ሥራ ይጠቅማታል ያለውን ከኢንተርኔት ላይ እያወረደ ይሰጣት ነበር። ቲያትር ወይም ፊልም ስራና ቀረፃ ኖሯት ስታመሽ እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ከእንቅልፉ ጋር እየታገለ በትግስት ይጠብቃት እንደነበርም ታወሳለች።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው የቲያትሩንና የፊልሙን ዓለም ከተቀላቀለች በኋላ ከጓደኞቿ ጋር የማታ ትምህርት ተምረው መሆኑን የምትናገረው አርቲስቷ ካገባች በኋላ ዕውቀቷን እንድትጨምር በማድረጉ ረገድም ባለቤቷ ሚናው የጎላ ነበርም ትላለች። ባህል ሚኒስቴር ለቲያትር ቤቶች በሰጠው ዕድል ዩኒቨርሲቲ ገብታ ሦስት ዓመት ተኩል ስትማርም እገዛው አልተለያትም።

ባለቤቴ በተፈጥሮ የሚገባው፣ አውቆት ሳይሆን በማንበብ ወይም ተመልካች ሆኖም የሚያውቅ ሰው ዓይነት ነው ትላለች። አንዳንድ ጊዜ ታዲያ የምትሰራውን ሥራ ታወራዋለች። ይሄ እንዲህ ቢደረግ ይሻላል ይላታል። ልጆቻቸው ከፍ ከፍ ካሉ በኋላ እረፍት በሆኑ ቀን ራት እንደሙብላት ወይም እንደሽርሽር ዓይነት ቦታ ተያይዘው ይወጡ ነበር። ለልጆቻቸውም እንዲህ ዓይነቱን ጊዜ ይሰጣሉ። ከባድ ሥራ በሚኖራት ጊዜ ባለቤቷ በደንብ ያውቃል። ስለዚህ በውጭ ምትሰማው ቢኖርም የቅናት ክፉ ስሜት እሷ ቤቷ ውስጥ ገብቶ አያውቅም። ጓደኞቿም አልገጠማቸው።

ራስ ቲያትር የነበርን ልጆች በሙሉ ከጓደኝነት አልፈን ልክ እንደቤተሰብ የምንተዋወቅ ነበርን። አንዱ አንዱ ቤት ይመጣል። የሌላውን ባል ወይም ሚስት ሌላው ያውቀዋል። የኛ ዘመን እንዳሁኑ ዓይነት አልነበረም። ምን አልባት ወደ ክፉ ሀሳብ የማንገባው ይሄ ነገር ረድቶን ይሆናል ብዬ አስባለሁ ትላለች ምክንያቱንም ስታብራራ።

አርቲስቷ እንዳወጋችን በእርግጥ ባለቤቷ የሚሰራው አዲስ አበባ ውስጥ ቢሆንም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ ነበር። ድርጅቱ ገባ ወጣ ብሎ የሚሰራበትም አልነበረም። ፈቃድም ቢሆን ከአቅም በላይ ካልሆነ አይሰጥም። በመሆኑም ልጆች መውለድ ብቻ ሳይሆን ማሳደግ፣ ለልጆች የበለጠ ጥንቃቄና እንክብካቤ ጥበቃ ሲባል ከሰራተኛ ጋር ወደ ወላጆች ቤት መውሰድ፣ ከፍ ሲሉም ትምህርት ቤት ማስገባት፣ ከቤት ወደ ትምህርት ቤት፣ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ማመላለስ፣ በትምህርት ቤት ያለውን መከታተል በእሷ ላይ ነበር የወደቀው። ‹‹እንደገና ቤቴ አለ። ቤቴ ውስጥ መአት ነገሮች ያስፈልጉኛል። እነዚህን ሁሉ የማሟላው እኔ ነኝ›› የምትለው ዓለምፀሐይ ይሄ ከከባዱና ፋታ ከማይሰጠው የቲያትርና ፊልም ሥራ ጋር ስደመር ሕይወቷን እጅግ ፈታኝ አድርጎት እንደነበርም ታወሳለች። በተለይ እስቴጅ (መድረክ) ላይ የነበረባትን ኃላፊነት ቤት ውስጥ ከነበረው ጣጣ ጋር አስታርቆ ለመሄድ ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል። ቤቷን የምታየው ከምሽቱ ስድስት እና ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ከሥራ ስትመለስ ነው። ሰርክ ባለቤቷ የቤት ሥራቸውን አሰርቶ ጠረጴዛ ላይ የሚያስቀምጥላትን የልጆቿን ደብተር ታያለች። ትምህርት ቤታቸው በሚጠይቀው መሰረት ፊርማዋን ከማሳረፏ በፊት በትክክል መሰራቱን ማረጋገጥም ግዴታዋ ነበር። በዚህም ለእንቅልፍ የምትሰጠው ሰዓት ሁለት ሰዓት ሆኗል። ምግብ የምታዘጋጅ ሰራተኛ ብትኖራትም ልጆቿ ዩኒቨርሲቲ እስኪገቡ ድረስ ምሳቸውን የምትቋጥረው ራሷ ነበረች። በመሆኑም በብዙ ደክማለች። ሆኖም የትኛውም የቲያትርም ሆነ የፊልም ሥራዋ ላይ ‹ያደረገባት ተፅዕኖ አልነበረም። መሸለም ያስቻላትም ይሄው ስኬቷ ነው። የእሷም ሆነ የሌሎች ሴቶች ስኬት ደግሞ ለሌሎች አርአያ ይሆንና ያነሳሳል። ሴት ትችላለች የሚለውን ያሳያል የሚለው ሀሳቧ ነው። መልካም ንባብ!

# ማረፊያ | አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ከ1950ዎቹ መባቻ ጀምሮ የነበሩ ጋዜጦች ተመልክተናል። ብዙዎቹ ጋዜጦች በወቅቱ ይዘው የወጡት ዜና ትንግርት ነክ ክስተቶች ነበሩ። እነዚህ ዜናዎች በጋዜጣው ሲዘገቡ ግን በአንድ አንቀጽ ብቻ የተገደቡ ነበሩ። እነዚህን ዘገባዎች ዛሬ ላይ ሆነን ስንመለከታቸው የአንባቢን ጥያቄ ወይም የዜናን መሥፈርት ሳያሟሉ ይችላሉ። በዚያን ወቅት የጋዜጠኝነት ሙያ በአገራችን ገና ካለመዳበሩ ጋር ተያይዞ ሲሆን ይችላል ዘገባዎቹ ሲነበቡ ከዚያስ፣ እና ምን ይጠበስ ? ሲያስብሉ የሚችሉ ናቸው። ያንን ዘመን ዛሬ ላይ ሆነን እንድናይ የሚያስችሉን አንድ የታሪክ አካል በመሆናቸው ግን ትንሽ ዘና ሲያደርጉን ይችላሉ ብለን በማሰብ እንደሚከተለው መርጠን ለትውስታ አቅርበናቸዋል።**

### ጎንደር
### በመብረቅ አደጋ የሞተ ወንጀለኛ

ጫቅሉ መስፍን የተባለው ወንጀለኛ በጎንደር አውራጃ አርማጭሆ ወረዳ ግዛት ውስጥ ጃግሬ ሚካኤል ቀበሌ አቶ ገበየሁ ካሣ የተባለውን ሰላማዊ ሰው መጋቢት በ ፲፩ ቀን ፴፱ ዓ.ም ከሌሊቱ ባልታወቀ ሰዓት ከመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እንደተኛ በግፍ በአንድ ጥይት ገድሎት አምልጦ ፖሊስ በጥብቅ በመከታተል ሐምሌ ፳፫ ቀን ላይ ሣለ ፴፱ ዓ.ም ከቀኑ ፲ ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ በዚሁ ወረዳ ግዛት ከች ባጀና በተባለ ምክትል ወረዳ ግዛት ውስጥ ከተደበቀበት ቦታ የመብረቅ አደጋ የገደለው መሆኑን ከጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ጽ/ ቤት ዋና ጸሐፊ ከመቶ አለቃ ግርማ እንዳልካቸው በደረሰን ወሬ ተገልጿል።

**የቤጌምድርና ስሜን አዛዥ አዛንስ**

**(ጳጉሜ ፪ ቀን ፴፱ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን )**

### ጅብን ከሰውና ውሻ ማላመድ

ፈሪነታቸው በወሎ ጠቅላይ ግዛት በደሴ ከተማ የሆነ አቶ በየነ ገብሩ የሚባሉ የጦር ሠራዊት ባልደረባ አንድ የጅብ ግልገል ከዱር አግኝተው ይዘው እቤት ካሏቸው ውሾች ጋር በማላመድ በዕረፍት ጊዜያቸው ውሻውንና ጅቡን ባንድ ጋሪ አሳፍረው ሲንሸራሸሩ ለሕዝብ ሲያሳዩ ይታያል።

ይህ ጅብ ስንት ጊዜ ከሳቸው ጋር እንደቆየ ብጠይቃቸው ጥቅምት ፲፩ ቀን ፩ሺህ፱፻፶ ዓ.ም ሲደርስ አንድ ዓመቱ መሆኑንና በዚህም ጊዜ ውስጥ በግልገልነቱ የከብት ወተት በጡጦ እየጠባ ከአደገ በኋላ ግን እንጀራ መመገቡን ገልጸውልናል። ከዚህም በላይ እርስዎ አንድ ወታደር ነዎት፣ ይህ ጅብ እንደ አንድ ቤተሰብ የምግብ ወጪ ይጠይቅዎታል፣ ደግሞስ ምን ሊሰጥዎት ነው እንዲህ የሚደክሙት ? ብዬ ብጠይቃቸው እንደሚከተለው መልስ ሰጥተውኛል።

ሰው በተስፋ ይኖራል፤ እኔም በወታደርነቴ መጠን ከማገኘው ደሞዝ ቀንሼ ይህን ጅብ በማሳደግ ከሰውና ከውሻ አላመድኩት፣ አሁን እርስዎ በእጅዎ ዳሠው እንዳዩት ሁሉ በሌላውም ዓለም ክፍል ብዙ ዓይነት የዱር አውሬዎች እንደዚሁ ለማዳ በመሆን ብዙዎች ለሥራ አገልግሎት ጥቅም ሲውሉ፣ ብዙዎቹ ደግሞ በአንድ ሥፍራ ተከማችተውና በደንብ ተይዘው ሰው ሠራሽ ቲያትርና ሲኒማ እንደሚታየው ሁሉ በእግዚአብሔር የተፈጠሩትን አውሬዎችና እንስሳዎች አብልጠው በማፍቀር አገር ጐብኚዎችም ሆኑ ተወላጆች እንደ ትንግርት ማየታቸውን ስለምሰማ፣ እንደዚህ ያለውን ለአገር ጥቅም መንግሥት ሳይከታተለው አይቀርምና በበላይ አለቆቼ አማካይነት አቅርቤ አንድ ሽልማት የማገኝ ስለመሰለኝ በተስፋ አሳድጋለሁ ሲሉ መልስ ከሰጡኝ በኋላ፣ እኔም በኚሁ አረጋዊ ሰው ሐሳብና ንግግር በመገረም አይቼና ሰምቼ ዝም ከማለት ያላዩ እንዲያዩ፣ ያልሰሙ እንዲሰሙ ስለሚያስፈልግ በዚሁ ዓምድ ለአንባቢዎች እገልጻለሁ።

**በየነ ዘመንፈስ**

**(መስከረም 16 ቀን 1950 ታትሞ ከወጣው አዲስ ዘመን)**

### የነፋስ ኃይልና ማዕበል

በፍቼ አካባቢ ደገም ምክትል ወረዳ ግዛት ውስጥ ሐምሌ ፲፱ ቀን ፩ ሺ፱፻፴፱ዓ.ም ከምሽቱ ፩ ሰዓት ላይ ነፋስ ተነስቶ የሰላሣ ቤቶችን ክዳን ገፎ ሣሩን ወዴት እንዳደረሰው አልታወቀም። ትልልቅ ዛፎችም ጥሏል። በሰው ላይ አደጋ አላደረሰም።

በዚሁ ሌሊት ውስጥ፤ በዚሁ ቦታ በቀኝ አዝማች ገለልቻ መልከኝነት ከባድ በረዶ ጥሎ እህልና አትክልት በጣም አጥፍቷል ሲሉ የወረዳው ገዥ ግራዝማች በቀለ አሽብር ነሐሴ ፲፰ ቀን ፩ ሺ፱፻፴፱ ዓ.ም በቁጥር ፩ሺህ ፱፻፶ በተጻፈ ደብዳቤ አረጋግጠውልናል።

**(መስከረም ፳፩ ቀን ፶ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### አንድ ጊደር መንታ ወለደች

በደገም ምክትል ወረዳ ልዩ ስሙ ቦስታ በሚባለው ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ አቶ አፈወርቅ ቸኮለ ነሐሴ ፲፯ ቀን ፴፱ ዓ.ም አንድ ጊደር ሁለት ጥጆች ወልዳ የተወለዱትም በሕይወት አሉ። ከብቷም ደህና ነች ሲሉ እመሥሪያ ቤታችን ድረስ መጥተው ገልጸውልናል ።

**(መስከረም ፳፩ ቀን ፶ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ባለ አራት እግር የዶሮ ጫጩት

በሐረር ከተማ ውስጥ ሸንኮር በሚባለው ሠፈር በማመድ ዩሱፍ ቤት አራት እግር ያላት የዶሮ ጫጩት ተፈልፍላ ኖሮ በመስከረም ፳፱ ቀን በ፶ ዓ.ም በክፍሉ ሠፈር ሹም አማካይነት በሙሳ ገበሬ እጅ ለሐረር ከተማ ሹምና አውራጃው ገዥ ድረስ መጥተው ከተመለከቷት በኋላ ለጊዜው ጫጩቷ ማዘጋጃ ቤት የቆየች መሆኗን ከሐረር ጠቅላይ ግዛት ማዘጋጃ ቤት የደረሰው ወሬ አረጋግጧል።

የሐረር ጠቅላይ ግዛት አዣንስ

**(ጥቅምት ፱ ቀን ፩ ሺህ ፱፻፶ ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ልጆች ለተጧሪዎች ልብስ ገዙ

አዲስ አበባ (ኢ-ዜ-አ-) በመካከለኛ ወረዳ ግዛት አካባቢ የሚገኙት ተማሪዎች በሠፈሩ ለሚኖሩት ተጠዋሪ ሽማግሌዎች ልብስ ገዝተው ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፷፩ ዓ.ም አለበሱ።

ተማሪዎቹ ለልብስ መግዣ ገንዘብ የሰበሰቡት በዕረፍት ጊዜያቸው በገዛ ኃጢያቴ ሲኦል ሆነ ቤቴ በሚል አርዕስት ያዘጋጁትን ቲያትር ለወላጆች በማሳየት ባገኙት ገቢ ነው። ከዚሁ ቲያትር ተማሪዎቹ ያገኙት ገቢ ፹፫ ብር ከ፷፫ ሳንቲም ሲሆን፤ ለአራት ችግረኛኞች ሽማግሌዎች የቀንና የሌሊት ልብስ ገዝተው አልብሰዋል።

ተማሪዎቹ ቲያትሩን ባሳዩበት ጊዜ በወረዳ ግዛቱ የተቋቋመው የዕድር ማኅበር ድንኳን በመስጠት የረዳቸው መሆኑ ተገልጧል። ከዚሁ በቀር ተማሪዎቹ ወላጆች ላደረጉላቸው ድጋፍና ርዳታ ምስጋና አቅርበዋል።

**(ጥቅምት 7 ቀን 1961 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ



ታይዋን በቅርቡ ወታደራዊ ልምምድ አድርጋለች

## ጆ ባይደን ቻይና በታይዋን ላይ ጥቃት ከፈጸመች አሜሪካ ታይዋንን እንደምትከላከል አስታወቁ

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ቻይና በታይዋን ላይ ጥቃት የምትፈጽም ከሆነ አገራቸው ታይዋንን እንደምትከላከል አስታውቀዋል።

ፕሬዚዳንት ባይደን ከሲ ቢ ኤስ ቴሌቪዥን ጋር በነበራቸው ቆይታ÷ አሜሪካ ከታይዋን ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከምትከተለው ፖሊሲ ያፈነገጠ ምላሽ ሰጥተዋል። ጆ ባይደን ቻይና በታይዋን ላይ ጥቃት የምትፈጽም ከሆነ አሜሪካ ታይዋንን ትከላከላለች ወይ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ “አዎ ትከላከላለች” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ከዚህ ባለፈም ጥቃት የሚፈጸም ከሆነ የአሜሪካ ወታደሮች ታይዋንን ለመከላከል በቀጥታ የሚሳተፉ መሆኑን ነው ያረጋገጡት።

የባይደንን ምላሽ ተከትሎም አሜሪካ በታይዋን ላይ የምታራምደው የአንድ ቻይና ፖሊሲ ማክበሯን አቁማለች በሚል ብዙዎችን አነጋግሯል። ከባይደን አስተያየት ጋር ተያይዞ ኋይትሐውስ በሰጠው ማብራሪያ÷ የአሜሪካ ፖሊስ እንዳልተቀየረ በማስረገጥ ከፕሬዚዳንቱ ምላሽ ጋር የሚቃረን ሃሳብ ሰጥቷል።

ቻይና በታይዋን ጉዳይ እንደማትደራደርና ውጊያ መግጠም ካለባትም ለመግጠም ዝግጁ መሆኗን በተደጋጋሚ ቤጂንግ አሜሪካን አስጠንቅቃለች። ታይዋን በምሥራቅ ቻይና የባሕር ዳርቻ ላይ የምትገኝ ራስ ገዝ ደሴት ስትሆን ቤይጂንግ የግዛቴ አካል ናት ስትል ትገልጻለች።

የዩናይትድ ስቴትስ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ናንሲ ፔሎሲ በነሐሴ ወር በደሴቲቱ ያደረጉት አወዛጋቢ ጉብኝት በአሜሪካ እና በቻይና መካከል ያለውን ውጥረት አባብሶታል። ባይደን ጉብኝቱን ቀደም ብለው “ጥሩ ሃሳብ አይደለም” ብለው ነበር። በምላሹ ቤይጂንግ በታይዋን ዙሪያ ለአምስት ቀናት የቆየ ወታደራዊ ከበባ በማድረግ ልምምድ አካሂዳለች። ቻይና “ለአሜሪካ ከባድ ማስጠንቀቂያ ነው” ያለችውንም ወታደራዊ ልምምድ በታይዋን አቅራቢያ ስታደርግ እንደቆየችም የሚታወስ ነው።

ዩናይትድ ስቴትስ ወደ ደሴቲቱ ሚሳኤል መተኮሱን ብትናገርም ቤይጂንግ ግን ይህንን አላረጋገጠችም። ቻይና የተኮሰችው ሚሳኤሎች ምንም አይነት ስጋት እንዳልፈጠሩ ታይዋን መናገሯ የቅርብ ጊዜ ክስተት መሆኑን ኤፍቢሲ ዘግቧል።



## ቻይና ከማርስ ያገኘቻቸውን ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶች ይፋ አደረገች

ቻይና በማርስ የጠፈር ምርምሯ ያገኘቻቸውን ውጤቶች ይፋ አደረገች። የቻይና ብሄራዊ የጠፈር አስተዳደር ይፋ ባደረገው ውጤት መሰረት የቻይና ተመራማሪዎች በማርስ አቀማመጥና አጠቃላይ ገጽታ አፈጣጠር እና በውሃ እንቅስቃሴዎች መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ገለፃ አድርገዋል።

ተመራማሪዎቹ በቀይዋ ፕላኔት ከ፣ ቢሊየን አመታት በፊት ጀምሮ የፈሳሽ ውሃ እንቅስቃሴ መኖሩን የሚያመላክቱ እርጥበት አዘል ማዕድኖች ማግኘታቸውን አስታውቀዋል። ባረፉበት የማርስ ክፍል የፕላኔቷ አፈር በውሃ እና በነፋስ መሸርሸር ሳያጋጥመው እንዳልቀረ የሚያመላክቱ ማስረጃዎችን አግኝተናልም ነው ያሉት።

በማርስ ላይ የሚገኘው አፈር ከፍተኛ እርጥበት የመሸከም አቅም እና ዝቅተኛ የእፍግታ መጠን እንዳለው አመላካች ውጤት ማግኘታቸውንም ገልጸዋል።

ከግኝታቸው በመነሳትም በፕላኔቷ ላይ ያለው የንፋስና የውሃ እንቅስቃሴ በማርስ ገጽታ ዝግመተ ለውጥ እና አካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ፥ በፕላኔቷ ላይ በሚገኘው ዩቶፒያን ፕላኒሺያ በተባለ ስፍራ ውቅያኖስ ነበር ለሚለው መላምት አጋዥ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም በማርስ ላይ ስላለው የድንጋይ ጥግግት እና የመሬት መሸርሸር መጠን እንዲሁም የማርስ የስበት መጠንን በተመለከተ በርካታ ሳይንሳዊ ውጤቶችን አግኝተናል ብለዋል።

የቻይና ብሄራዊ የጠፈር አስተዳደር ለወደፊት ፕላኔቷን በተመለከተ የርቀት ዳሰሳ ጥናቶችን እና ሳይንሳዊ መረጃዎችን መሰብሰቡን እንደሚቀጥል ማስታወቁን ሲ ጂ ቲ ኤን የዘገበውን ኤፍቢሲ ጠቅሶ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በጎዳና ላይ ውድድሮች ድል ቀንቷቸዋል

**ብርሃን ፈይሳ**

ያለንበትን መስከረም ወር ጨምሮ መጪዎቹ ጥቂት ወራት በመላው ዓለም የጎዳና ላይ ውድድሮች በስፋት የሚካሄዱበት ነው። በየሳምንቱ መጨረሻ በሚካሄዱ የሃያ አንድ ኪሎ ሜትር እና የተለያዩ የማራቶን ውድድሮች ላይም ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች የተለመደ ድላቸውን እያስመዘገቡ ይገኛሉ። ከትናንት በስቲያ በዴንማርክ ኮፐንሃገን በተካሄደው ግማሽ ማራቶን ውድድርም ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በሁለቱም ጾታ አሸናፊዎች በመሆን እንደተለመደው የአገራቸውን ስም አስጠርተዋል። ውድድሩ በዓለም አትሌቲክስ የኤሊት ደረጃ የተሰጠውም ነው።

ፈጣን በነበረው በዚህ ውድድር ላይ 15 የሚሆኑ አትሌቶች ከ1 ሰዓት በታች ውድድራቸውን መፈጸም እንደቻሉም ነው አወዳዳሪው አካል ያስታወቀው። በወንዶች በኩል በተካሄደው ውድድር ሚልኬሳ መንገሻ የአገሩን ልጅ አስከትሎ በመግባት አሸናፊ ሆኗል። እአአ በ2019 ከ20 ዓመት በታች አገር አቋራጭ ቻምፒዮን የነበረው ሚልኬሳ ይህንን ርቀት ለመጨረስ የፈጀበት ሰዓት 58:58 ሆኖ ተመዝግቧል። እስከ 15ኛው ኪሎ ሜትር ድረስ በምስራቅ አፍሪካዊያን ተፎካካሪዎች ተከቦ የሮጠው አትሌት ሚልኬሳ አፈትልኮ በመውጣትና ሩጫውን በማፍጠን ባለድል መሆኑን አረጋግጧል።

እርሱን ተከትሎም እጅግ ተቀራራቢ በሆነ ሰዓት የአገሩ ልጅ አምደወርቅ ዋለልኝ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ማጠናቀቅ ችሏል። ለአሸናፊነት በተለይ ሲፎካከር የቆየው ይህ አትሌት የገባበት ሰዓት በአንድ ደቂያ ዘግይቶ 59:05 ተመዝግቧል። የኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ቀዳሚ ተፎካካሪ የሆኑት ኬንያዊያን አትሌቶች ደግሞ ሶስተኛ እና አራተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን አጠናቀዋል። ሶስተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀው ፍሌክስ ኪፕኮች ለአምደወርቅ ፈታኝ ተፎካካሪው ሆኖ በውድድሩ ላይ የታየ ሲሆን፤ ያስመዘገበው ሰዓትም ከኢትዮጵያዊው አትሌት በሁለት ሰከንዶች ብቻ የዘገየ 59:07 ነው። ሌላኛው ኬንያዊ ቪንሰንት ኪፕኬሞይ ደግሞ 59:09 በሆነ ሰዓት አራተኛ ሆኗል።




**ወጣቶቹ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ሚልኬሳ መንገሻና ታዱ ተሾመ በኮፐንሃገን ግማሽ ማራቶን ፈጣን ሰአት በማስመዝገብ አሸንፈዋል፣**

በሴቶች በኩልም በተመሳሳይ የበላይነቱ በኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ሲያዝ፤ አትሌቶቹ የገቡበት ሰዓት እጅግ ተቀራራቢ መሆኑ ብርቱ ፉክክር ማድረጋቸውን ያመላከተ ነበር። አሸናፊዋ አትሌት ታዱ ተሾመ የግሏን ፈጣን ሰዓት ያሻሻለችበት ውድድርም ነው። ውድድሩ ከመነሻው አንስቶ በታዱ እና በሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ጽጌ ገብረሰላማ ሲመራ የቆየ ሲሆን፤ ከ15ኛው ደቂቃ በኋላ ግን ታዱ ፈጥና በመሮጥ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ወደ 30 ሰከንድ ማስፋት ችላለች። በዚህም አሸናፊዋ አትሌት የገባችበት ሰዓት 1:06:13 ሆኖ ተመዝግቧል።

ለማሸነፍ ብርቱ ፉክር ስታደርግ የቆየችው ጽጌ በበኩሏ ልዩነቱን ወደ 22 ሰከንዶች በማጥበብ 1:06:35 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ በመሆን ውድድሩን አጠናቃለች። ሌላኛዋ አትሌት ጥሩዬ መስፍንም ከአገሯ ልጆች ሰከንዶችን ብቻ በመዘግየት 1:06:42 በሆነ ሰዓት ሶስተኛ ደረጃን መያዝ ችላለች።

ሌላኛው በሳምንቱ መጨረሻ የተካሄደና ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ቀዳሚ በመሆን ያጠናቀቁበት ውድድር ደግሞ በአውስትራሊያ ሲድኒ የተካሄደው የማራቶን ውድድር ነው። በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ተከታትለው ሲገቡ፤ አንዲት ኤርትራዊ አትሌትን በመሃል በማስገባት እስከ ስድስት ያለውን ደረጃ ይዘው ጨርሰዋል። 2:25:10 በሆነ ሰዓት ቀዳሚ የሆነችው አትሌት ትዕግስት ግርማ፤ ከሃገሯ ልጅ ለተብርሃን ኃይላይ ጋር ከፍተኛ ፉክክር አድርጋለች። በዚህም ለተብርሃን በሰከንዶች ብቻ ተበልጣ 2:25:45 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ ደረጃን ልትይዝ ችላለች። ሶስተኛ የሆነችው ኤርትራዊት አትሌት ናዝሬት ወልዱ በ2:26:14 ገብታለች። ራህማ ቱሳ፣ የኔነሽ ጥላሁን እና ፋንቱ ጂማ ደግሞ እስከ ስድስት ባለው ደረጃ ተከታትለው የገቡ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ናቸው።

በተመሳሳይ በወንዶች መካከል እጅግ ፈታኝ በነበረው ውድድር አራት አትሌቶች ለአሸናፊነት ከፍተኛ ትግል ያደረጉ ሲሆን፤ በማራቶን ውድድር ብዙም ባልተለመደ ሁኔታ አንገት ለአንገት ተያይዘው በመግባት በሰከንዶች ብቻ ተለያይተው ማጠናቀቅ ችለዋል። አሸናፊው አትሌት ኬንያዊው ሞሰስ ኪቤት 2:07:03 በሆነ ሰዓት በመግባት በአውስትራሊያ ፈጣኑን የማራቶን ሰዓት ሊያስመዘግብ ችሏል። ሌላኛው ኬንያዊ ኮስማስ ማቶሎ ደግሞ 2:07:05 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ ሆኗል። በሶስት ሰከንዶች የዘገየው ኢትዮጵያዊው ጫሉ ዴሶ 2:07:08 ሶስተኛ ሲሆን፤ አበበ ነገዎ 2:07:26 በሆነ ሰዓት አራተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል። አሊቃ አዱኛ ደግሞ ከአራት ደቂቃዎች በኋላ አምስተኛ ደረጃን ይዞ ያጠናቀቀ ኢትዮጵያዊ አትሌት ሆኗል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission (ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# ብራንድ የተደረገው የቦንጋ በግ

**በአለምነህ ቸርነት**

በኢትዮጵያ 31 ነጥብ 30 ሚሊዮን የበግ ብዛት እንዳለ ይገመታል። ኢትዮጵያ ካላት የበጎች ብዛት 75 በመቶ ያህሉ በደጋው የአገሪቱ ክፍል ሲገኝ ቀሪው 25 በመቶ ደግሞ በቆላማ አካባቢዎች የሚገኙ ናቸው። በዝርያ ደረጃ በአገራችን ካለው የበግ አይነት ውስጥ 99 ነጥብ 81 በመቶ የሚሆነው አገር በቀል ዝርያዎች ናቸው። እነዚህ ዝርያዎች በዋና ዋና የአገሪቱ የአግሮ-ኢኮሎጂካል ዞኖችና ጂኦግራፊያዊ ክልሎች ተሰራጭተው ይገኛሉ። የቦንጋ በግ ዝርያ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በመካከለኛና ከፍተኛ ቦታዎች ይገኛል።

የቦንጋ በግ በአገራችን ከታወቁ የበግ ዝርያዎች መካከል አንዱ ነው። የቦንጋን በግ ለማርባት ምቹ ከሆኑት ባህሪዎቹ አንዱ እድገቱን ጨርሶ ለገበያ ለመቅረብ የሚወስድበት ጊዜ በአንጻራዊነት አጭር የሚባል በመሆኑ በጣም ምርታማ ነው። በዚህም የተነሳ በግ በማድለብ ሥራ ለሚሰማሩ አካላት በቀላሉ በአጭር ጊዜ ለማድለብ የሚመች የበግ ዝርያ ዓይነት ነው። የቦንጋ በግ አጥንት ቅርጽ ከሌሎች የኢትዮጵያ የበግ ዝርያዎች ጋር ሲነጻጸር ትልቅና በሽታዎች የመቋቋም አቅም አለው።

በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የካፋ ዞን የቦንጋ በግ በስፋት ለማርባትና ለገበያ ለማቅረብ ተስማሚ የአየር ሁኔታና ከዓመት ዓመት የማያቋርጥ ዝናብ ያለው በመሆኑ ለመኖ/ሣር/ ምርት አመቺ ነው። በአሁኑ ግዜ የቦንጋ በግ እርባታ ከዓመት ዓመት እየጨመረ ሲሆን በ2014 ዓ.ም 173 ሺ 200 በጎች እንደረቡና በዚህው ዓመት በበግ እርባታ የተሰማሩ የበግ አርቢዎች ብዛት 314 ሺ 909 መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ።




በክልሉ የበግ እርባታ ጥራትን ለማስጠበቅ በኤክስቴንሽን ዘርፍ ከምርምር ተቋማት ጋር በመሆን በተመረጡ ኮርማዎችና እናት በጎች ዝርያዎችን በማሻሻል ምርጥ የተሻሻለ የቦንጋ በግ ዝርያን ለማስፋፋት ጥረት እየተደረገ ይገኛል። አርሶ/አርብቶ አደሩ አብዛኛውን ግዜ ባህላዊ የአመጋገብ ዘዴ የሚተገብር ቢሆንም አሁን ላይ የተሻሻሉ መኖዎችን አቀናጅቶ በመጠቀም ላይ ይገኛል። የበግ ጤንነትን በማስጠበቅ ረገድ ክትባት የመስጠትና በሽታ ሲከሰት የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ ስራ እየተከናወነ ነው።

የቦንጋ በግ ጣፋጭና ለስላሳ ሥጋ ያለው ባለ ከፍተኛ ጥራት ዝርያ ነው። የቦንጋ በግ የቆዳ ቀለም ቀይ ቡናማ ሲሆን ረጅም ቀጥ ያለ የሰባ ላትና ረጅም ጆሮ ያለው ነው። የቦንጋ በግ ሲወለድ ያለው ክብደት ከሌሎች ዝርያዎች አንፃር ከፍ ያለ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

የቦንጋ በግ ብራንድ እንዲሆን ከላይ ከተገለጹት አስቻይ ሁኔታዎች በተጨማሪ ዝርያውን የበለጠ ለማሻሻል በምርምር የተጀመረ ሥራ መኖሩ፣ የአርሶ/አርብቶ አደሩ ጠንካራ የማርባት ልምድ፣ በአብዛኛው ሁለትና ከዚያ በላይ መውለድና በፍጥነት ማደግ የሚችሉ መሆናቸው፣ በተወለዱ ሶስት ወር አማካይ ክብደታቸው ከ16 ኪሎ ግራም በላይ መሆን መቻሉ፣ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሶስት ጊዜ መውለድ መቻላቸው፣ ኮርማው ከአምስት እስከ ስድስት ወርና ሴት/ጊደር/ከስድስት እስከ ስምንት ወር ለጥቂ መድረሳቸው የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው።

ቀደም ባሉት ዓመታት በከፋ ዞን የነበረው በግ የማርባት ዓላማ አሁን ላይ ተቀይሮ አርሶ/አርብቶ አደሩ የቦንጋ በግ የሚያረባው በቀዳሚነት ለገቢ ማስገኛ ሲሆን በመቀጠል ለቤት የምግብ ፍጆታ ሆኗል። የቦንጋ በግ በአገራችን በአብዛኞቹ ክልሎች ለዝርያ ማሻሻያና በቁም ከብት ነጋዴዎች ደግሞ ለሥጋ ገበያ እየቀረበ ይገኛል። አዲስ አበባ፣ አጎራባች ዞኖችና ክልሎች የቦንጋ በግ የገበያ መዳረሻዎች ናቸው። ሆኖም ግን ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር ለመፍጠር ገና ብዙ ስራ የሚጠይቅ መሆኑ የተደረጉ ምልከታዎች ያሳያሉ።

አርሶ/አርብቶ አደሩን በኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀት ጉልህ ጠቀሜታ ያለው ነው። አንድም አምራቾች የኤክስቴንሽን አገልግሎትና የተሻሻሉ ዝርያዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የገበያ መረጃ እንዲኖር በማስቻል የግብይት ወጪና የዋጋ መዋዠቅ ስጋት በመቀነስ የአምራቾችን ዋጋ የመደራደር አቅም የሚያጎለብት ነው። በዚህም መሰረት በክልሉ የቦንጋ በግ ዝርያ ምርታማነትን ለማሻሻል አስራ ስድስት (16) የቦንጋ በግ ዝርያ ማሻሻያ ኅብረት ሥራ ማህበራት በካፋ ዞን ተደራጅተው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ኅብረት ሥራ ማህበራት የበግ ዝርያውን በማሻሻልና የአምራቾችን ገቢ በማሳደግ ረገድ ስኬታማ መሆን እንደቻሉ ጥናቶች አመላክተዋል። እንዲሁም ያሉትን ኅብረት ሥራ ማህበራት ማጠናከርና አዳዲስ ተጨማሪ ኅብረት ሥራ ማህበራትን ደግሞ ማቋቋም አስፈላጊ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል።

የቦንጋ በግ በአገራችን ካሉት ሌሎች የበግ ዝርያዎች ጋር ሲነጻጸር ተፈላጊነቱ በአገር አቀፍ ደረጃ እያደገ የመጣና ከፍተኛ የገበያ ዋጋ ያለው ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት የበግ ዋጋ ከሚተመንባቸው ባህርያት መካከል ዋናዎቹ ዕድሜ፣ ቀለም፣ የላት አይነት፣ ጾታ፣ የቀንድ አይነትና የሰውነት ስባት ሁኔታ ይጠቀሳሉ። በእነዚህ ባህርያት መሰረት ቀይ ቡናማ የቆዳ ቀለም፣ የሰባ ላትና ቀንድ አልባ በግ ያለው በግ ከፍተኛ ዋጋ እንደሚያወጣ በጥናት ተረጋግጧል። እነዚህን ተፈላጊ ባህርያት መሰረት ያደረገ ገበያ መር የበግ እርባታ ስርዓት መከተል አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ ተገቢነት ያለው የበግ እርባታ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ አስፈላጊ የመራቢያ ቦታ መምረጥና በቂ የመኖ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግና የመኖ አመጋገብ ስርዓትን ማስተካከል ያስፈልጋል።

የቦንጋ በግ ምርታማነትንና የግብይት ልማትን የበለጠ ለማሳደግ አንዳንድ ችግሮች ይስተዋላሉ። በምርምር የተጀመረ ሥራ በኤክስቴንሽን ዘርፉ በስፋት ያለ መስራት፣ በየቀበሌው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ያለመሟላት፣ ኅብረት ሥራ ማህበራት በዩኒየን አለመደራጀታቸውና ቀጣይነት ያለው የገበያ ትስስር ያለመኖር ያሉትን ችግሮች በቀጣይ መፍታት የሁሉም ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ